# ለችግር ተጋላጭና ተጎጅ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች

# የድጋፍና አገልግሎት አሰጣጥ

## መመሪያ ቁጥር 189/2018

## መግቢያ

ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭና ተጎጅ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ አገልግሎት ግልጽ፣ ወጥ፣ ፍትሀዊ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ እና ሕፃናቱ ሁሉን ዓቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ አግኝተው ደህንነታቸው፣ መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው ተጠብቆላቸው እንዲያድጉ በማስቻል ንቁ እና ጤናማ ዜጋ ለማፍራት እና የማኅበራዊና ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ሌሎች ለማኅበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ በሚደረግ ሂደት በቢሮው ውስጥ በሚገኙ የሥራ ክፍሎች መከካል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት ለተቃሚዎች ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት ማቅረብ የሚገባ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ሴቶች፣ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 33 እና በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ መመሪያ **"ለችግር ተጋላጭና ተጎጅ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የድጋፍና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር** 189/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው፡፡
2. **"ምክር ቤት"** ማለት በከተማ፣በክፍለ ከተማ፣በወረዳ እና በብሎክ ደረጃ የተቋቋመ ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀት ነው፤
3. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016 ነው፤
4. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ሴቶች፣ ህፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ነው፤
5. **"ድጋፍ''** ማለት ተጠቃሚ ለሚሆኑ አካላት በጊዜያዊና በዘለቄታ ከችግራቸው እንዲላቀቁ የጉልበት፣ የእውቀት፣ የገንዘብ እና በዓይነት የሚደረግ አስተዋጽኦ ነው፡፡
6. **"ተጠቃሚ''** ማለት ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ የግለሰቦች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤
7. **"ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ነዋሪ የሆኑና መደበኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ የገቢ ምንጭ የሌላቸው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ፣በሚደረግላቸው ልዩ ድጋፍ ስራ በመስራት ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር የሚችሉ፣ህጋዊ ሆነው በማህበር ተደራጅተው ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ ናቸው፡፡
8. **"ቀላል ተስማሚ ቴክኖሎጂ"** ማለት የዕደ ጥበብ ማምረቻና የምግብ ማምረቻ ቀላል ተስማሚ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ነው፤
9. **"አደረጃጀቶች"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተደራጅተው ወይም ተሰማርተው ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው የሴት አደረጃጀት ናቸው፤

10. “**ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች**” ማለት መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውና መብቶቻቸውን ማሟላት ያልቻሉ ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ በወሲብ የሚተዳደሩ፣ የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚዎች፣ለከፋ የምግብ ችግር የተጋለጡ ፣ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች፣ለምኖ አዳሪዎች ናቸዉ፡፡
11. “**ተጎጂ**'' ማለት ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤
12. “**ማዕከል**” ማለት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት እንዲሰጥ በአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሥር የሚተዳደር ማዕከል ነው፤
13. “**ወደ ቤተሰብ መልሶ ማቀላቀል**” ማለት ከወላጆቻቸው ወይም ከተቋጥሮ ቤተሰብ አባላት የተለዩ፣ ወላጅ ያጡ፣ ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት ለተገቢ ዕድገታቸው እንደገና በቤተሰብ ውስጥ ዘላቂና ቋሚ በሆነ መልኩ የሚያድጉበት ሁኔታ የማመቻቸት መር-ሃግብር ነው፤
14. “**ዳግም ወደ ማህበረሰቡ ማዋሐድ**” ማለት ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆናቸው የግላቸውን ሕይወት መምራት የሚፈቅድላቸው ታዳጊዎች ወደ ማህበረሰቡ እንዲዋሐዱ ሁኔታዎችን የሚያመቻች መርሃ ግብር ነው፤
15. “**ማቋቋም**” ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ ወይም ችግር ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ተሻለ ህይወት እንዲመለሱ በጊዚያዊነት ወይም በዘላቂነት የመደገፍና ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ነው፤
16. “**ስንብት**” ማለት አንድ ለችግር የተጋለጠ ሕፃን ወይም ለማኅበራዊ ችግር ተጋላጭ ሆነው በማዕከላት የሚገኙ ተገልጋዮች በተንከባካቢ አካላት የሚደረግን የገንዘብ ወይም የዓይነት ወይም የሁለቱም ድጋፍ በሚታወቅና ግልጽ በሆነ ምክንያት ተጠቃሚዎች ከድጋፍ አገልግሎቱ ማስወጣት ወይም ድጋፉን ማቋረጥ ወይም በማዕከላቱ በሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት የሚሰናበትበት አግባብ ነው፤
17. “**አካላት**” ማለት ከሠራተኞቻው ደመወዝ በፈቃደኝነት አንድ መቶኛ በሚዋጣ ገንዘብ ወይም ከድርጅታቸው በፈቃደኝነት በሚለገስ የገንዘብ ድጋፍ ለችግር የተጋለጡ ሕፃናትን የሚደግፉ መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ነው፤

18. **“የገቢ ማስገኛ ስራዎች”** ማለት የሥራ እድሎችን በመፍጠርና ከጥገኝነት በመላቀቅ የራስን ገቢ ማግኘት የሚያስችሉ የስራ ዘርፎች ነው፤
19. **“ወላጅ”** ማለት የሕፃኑ የተፈጥሮ እናትና አባቱ ወይም በህግ የወላጅነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤
20. **“ተንከባካቢ”** ማለት የአንድ ሕፃንን ደህንነት ለመጠበቅ በሕግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ነው፤
21. **“ወላጁን ወይም ወላጆቹን ያጣ ሕፃን”** ማለት እድሜው ከ18 ዓመት በታች ሆኖ አንድ ወይም ሁለቱም ወላጆቹን በማንኛውም ምክንያት በሞት ያጣ ሕፃን ነው፤
22. **“ክብካቤ”** ማለት ሕብረተሰብን መሠረት ያደረገ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ-ልቦናዊ አገልግሎቶችን በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር ለተጋለጡ ሕፃናት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤
23. **“የመብት ጥሰት”** ማለት ማንኛውንም አይነት የአሁን ወይንም የወደፊት አሉታዊ ተፅዕኖ በሕፃናት ኣ-ካል፣ አዕምሮ፣ እና ስሜት እድገት ላይ ሊያደርስ ወይንም ሊያስከትል የሚችል ድርጊት ነው፤
24. **“ጥቃት”** ማለት በአደራ የተሰጡ ሕፃናት ላይ የሚደርሱ አካላዊ ቅጣት፣ ወሲባዊ፣ የጉልበት ብዝበዛ፣ ሥነ-ልቦናዊ (ስድብ፣ ማንቋሸሽ እና የመሳሰሉት) ፣ ቸል መባል፣ ያለፈላጎት ለሦስተኛ አካል ተላልፎ መሰጠት፣ ምግብ መከልከል፣ የጤና እንዲሁም የንጽሕና ጉድለትን የመሳሰሉ ችግሮች ነው፤
25. **“ልዩ ፍላጎት”** ማለት በመወለድ ወይንም ከመወለድ በኋላ በልጆች ላይ የሚከሰትን የሚታይ ወይንም የማይታይ የመደበኛ ተግባር ውሱንነት ማለት ሲሆን የማየት፣ የመስማት፣ የመንቀሳቀስ፣ የመረዳት ወይንም ትምህርት የመቀበል እንዲሁም በልዩ ልዩ ሁኔታ በሃይለ-ስሜት ላይ ሊገለጡ የሚችሉ ውሱንነቶችን ያካትታል፤
26. **“የድጎማ አደራ ቤተሰብ”** ማለት ለአደራ ብቁ የሆነን ሕፃን ተቀብሎ በቢሮ ድጋፍ እየተደረገለት በማሳደግ ላይ የሚገኝ ቤተሰብ ነው፤
27. **“ቀጥታ ድጋፍ”** ማለት አልሚ ምግብ/ የተመጣጠነ ምግብ ከእርግዝነ ጀምሮ እስከ 6 ዓመት እድሜ ድረስ የሕፃኑን አካላዊ አእምሮ አዊ እንሁም ሁለንተናዊ እደገት ወሳኝ የሆኑ ምግቦችን እዲያገኙ ማድረግ ነው፤
28. **“ማቀላቀል”** ማለት ከሚኖሩበት ማህበረሰብና አካባቢ በተለያየ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ የተለያዩ የህብረተሰብ

ክፍሎችን ወደ መጡበት አካባቢና ማህበረሰብ በመመለስ ተረጋግተው እንዲኖሩ ማድረግ ነው፤

29. **"ጎዳና ተዳዳሪ"** ማለት ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ሰዎች ነው፤
30. **"ማኅበራዊ ችግር"** ማለት የማህበረሰባችን እድገት የሚያደናቅፍ ወይም የሚገድብና በቂ የኑሮ ደረጃን ማግኘት አለመቻል ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው፤
31. **"አረጋዊያን"** ማለት እድሜአቸዉ 60 አመትና በላይ የሆናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤
32. **"የወሲብ ተዳዳሪ"** ማለት ወሲብን እንደ ገቢ ምንጭ በመቁጠር በስምምነት ግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በመፈጸም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ ገቢ የምትተዳደር ሴት ነች፤
33. **"የከፋ የምግብ ችግር ያለባቸዉ"** ማለት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች መሰረታዊ ፍላጉት የሆነዉን የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት ያልቻሉ ነዋሪዎች ናቸው፤
34. **"የመብት ማህበራት"** ማለት በግለሰቦች ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ የአባላቱን ተፈጥሮዊና በህግ የተሰጣቸውን መብት ለማስከበር የተቋቋመ የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ማህበር ነው፤
35. **"የባይተዋር ቀብር አገልግሎት"** ማለት በማንኛውም ሁኔታ የቀብር አገልግሎት ማግኘት ለማይችሉሰዎች የሚሰጥ የቀብር አገልግሎት ነው፤
36. "ለድጋፍ የተሰበሰበ **ሀብት**'' ማለት ለተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሚሰበሰብ የጉልበት፣ የእውቀት፣ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ነው፤
37. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
38. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የገለጸው አገላለጽ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከማዕከል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር፣ በስሩ በሚተዳደሩ ተቋማት፣ እና የድጋፍ አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **<u>የመመሪያ ዓላማ</u>**

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1/ ለሴቶች የሚደረገው የገንዘብና ቁሳቁስ ድጋፍ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ችግራቸውን አጣርቶ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግ እና ወጥነት ያለው የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የኢኮኖሚ አቅማቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡

2/ የጊዜያዊ ማቆያና ማቋቋሚያ ተቋም አሰራር በሌሎች የሕፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጭ አገልግሎቶች ሊረዱ ያልቻሉትን ወላጅ ያጡና ለከፋ ችግር ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ ሕፃናትን መሰረታዊ የሕፃናት ፍላጎት መሰረት በማድረግ ተጠቃሚ ለማድረግና በሕፃናት ማሳደጊያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራትና ደረጃን ለማሻሻል እንዲረዳና በሕፃናቱ ህይወት ላይ የሚጠበቀውን ለውጥ ማምጣት ነው፡፡

3/ የገቢ መጠናቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ነፍሰ-ጡር ሴቶች፣ አጥቢ እናቶች እና እድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሚደርሱ የአልሚ ምግብ ድጋፍ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሕፃናት ንቁና ብቁ ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ ለማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ለሴቶች ስለሚደረግ ድጋፍ

5. **ሴቶች ልዩ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስፈልግ መስፈርቶች**
   1. ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሞላቸው እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ ስለመሆናቸው የወረዳ አስተዳደር መታወቂያ ወይም ከተለያዩ አደረጃጀቶች ወይም ሲቪክ ማህበራት በጽሁፍ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
   2. ከሚኖሩበት ወረዳ እና ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወይም ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
   3. የልዩ ድጋፍ ፈላጊዎች ሙሉ አድራሻ የቤተሰብ ብዛትና ሁኔታ መገለጽ አለበት
   4. ከዚህ በፊት በሌላ ድርጅት ወይም ተቋም በተመሳሳይ ድጋፍ ውስጥ ታቅፈው ድጋፍ እየተደረገላቸው እንዳይሆን ለድጋሚ ተጠቃሚነት አለመለየታቸው ከሚኖሩበት ወረዳ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
6. **ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች የክፍያ እና የቁሳቁስ ድጋፍ አሰጣጥ ሒደት**
   1. ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ባሉ መዋቅሮች ወይም በሚቋቋመው ኮሚቴ የማጣራት ስራ ከተደረገ በኋላ በቢሮው የበላይ ኃላፊዎች ቀርቦ ሲፀድቅ ብቻ ድጋፉ ይሰጣል፣
   2. ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው በፀደቀው ዓመታዊ የስራ ፕሮግራም መሰረት ለልዩ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የሚሰጥ ሲሆን አከፋፈሉም በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ሕግና አሠራር መሰረት ይሆናል፤
   3. የቁሳቁስ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት በከተማ ንብረት አስተዳር ሕግ አሰራር መሰረት ይሆናል፣
7. **ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መጠን**
   1. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ሴቶች ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ተስማሚ ቴክኖሎጅ ግዥ ፈጽሞ ለማሰራጨት የሚያስፈልግ መነሻ የገንዘብ መጠን ለአንድ (1) ሰው ብር 25,000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መጠን ሆኖ ከቁሳቁስ ግዥ የሚተርፈው ገንዘብ ለተጠቃሚዋ የሥራ ማስጀመሪያ እንዲሆን በተጠቃሚዋ ስም

በሚከፈተው አዲስ የባንክ ደብተር በቢሮው ፋይናንስ በኩል ገቢ የሚደረግላት ይሆናል፤

2. በጋራ ተደራጅተው ለመስራት ፍላጎት ያላቸውና የስራና የንግድ ክህሎት ስልጠና ወስደው አዋጪ በሆነ የስራ መስክ መሰማራት ለሚፈልጉማህበራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለአንድ (1) ሰው ብር 25,000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) የሚደረገው ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ከማህበሩ የቁሳቁስ ግዥ የሚተርፈው ገንዘብ ለማህበሩ የሥራ ማስጀመሪያ እንዲሆን በማህበሩ ስም በሚከፈተው አዲስ የባንክ ደብተር በቢሮው ፋይናንስ በኩል ገቢ የሚደረግ ይሆናል
3. በጋራ ተደራጅተው ለመስራት ፍላጎት ያላቸውና የስራና የንግድ ክህሎት ስልጠና ወስደው አዋጪ በሆነ የስራ መስክ መሰማራት ለሚፈልጉ ማህበራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለአንድ (1) ሰው ብር 25,000.00 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) የሚደረገው ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ከትረስት ፈንድ እና ከብድርና ቁጠባ ተቋማት በማፈላለግ ሴቶችን በማህበር አደራጅቶ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፤

8. <u>በየደረጃው ያሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት ተግባር</u>

1. በየደረጃው ያሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት በጋራ ወይም በተናጠል የሚከተሉት ተግባሮች አላቸው፡-ቢሮው የድጋፉን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ በበላይነት ይመራል፤
2. ቢሮው ለተጠቃሚ ሕፃናት ድጋፉ በትክክል መድረሱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. ቢሮው ለድጋፍ የተለዩ ሕፃናት በመስፈርቱ መሠረት የተለዩ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. የክፍለ ከተማ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት በወረዳ ደረጃ ተለይተው ለድጋፍ የሚለዩ በመስፈርቱ መሠረት የተለዩ መሆኑን ያረጋግጣል፣
5. የወረዳ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት በቢሮው ወይም በድርጅቶች ወይም በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ደረጃ ያለ ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልግ ድርጅት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ለችግር ተጋላጭ ሕፃናት ተለይተው እንዲላኩ ሲጠየቅ ለጠየቀው አካል በመለያ መስፈቱ መሠረት ያሳውቃል፡፡
6. በየደረጃው ያለው የሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ መዋቅር እንደየሚደግፋቸው ተጠቃሚ ሕፃናት የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ በአግባቡ ለተጠቃሚዎች ደርሶ ጥቅም ላይ መዋሉን ወርደው ሪፖርት አዘጋጅው ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

1. ማንኛውም ተጠቃሚ ሁለት ጊዜ በመመዝገብ በድጋሚ ድጋፍ መውሰድ አይችልም፤
2. ሀሰተኛ መረጃዎችን በማቅረብ የድጋፍ ተጠቃሚ መሆን ክልክል ነው፤
3. የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፉን ከታለመለት ዓላማ ውጪ መጠቀም የተከለከለ ነው፤
4. ማንኛውም ግለሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ማስተጓጎል የለበትም፤
5. በሥልጣን፣ በዘር፣ በዝምድና፣ በትውውቅ ወይም በሃይማኖት መሰረት በማድረግ አድሎአዊ አሰራር መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

# ክፍል ሶስት

# ለችግር ለተጋለጡ ሕፃናት ስለሚደረጉ ድጋፎች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ለሕፃናት ስለሚደረገው ድጋፍ

10. ድጋፉ ተጠቃሚ ሕፃናቱ መመልመያ መስፈርት

1) የድጋፉ ተጠቃሚ ሕፃናት ሲሆኑ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከ1-3 የሕፃናት ብዛት ያላቸውና ወርኃዊ የገቢያቸው መጠን ከብር 1500.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ) ያልበለጠ ሆኖ ሌላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ገቢ የሌላቸው ከሆኑ፤ ወይም
2) ከ 4-5 የሕፃናት ብዛት ያላቸውና ወርኃዊ የገቢያቸው መጠን ከብር 2000.00 (ሁለት ሺህ ብር) ያልበለጠ ሆኖ ሌላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ገቢ የሌላቸው ከሆነ፤ ወይም
3) ከ5 በላይ የሕፃናት ብዛት ያላቸውና ወርኃዊ የገቢያቸው ከብር 3000.00 ብር (ሦስት ሺህ ብር) ያልበለጠ ሆኖ ሌላ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ገቢ የሌላቸው ከሆኑ እና ምንም ዓይነት ተጨማሪ ንገቢ የሌላቸው ወይም በተመሳሳይ ድጋፍ ያልታቀፉ ቤተሰቦች መሆናቸው በሚኖሩበት አከባቢ ቢያንስ ለ6 ወራት የኖሩ ሕፃናት ሆነው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መሥፈርቶች መካከል ቢያንስ ከአራት (4) በላይ የሚያሟሉ ከሆነ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡
4) አንድ ወይም ሁለቱንም ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ከሆኑ፣
5) ወላጅ የአእምሮ ታማሚ ከሆነ ወይም ሥራ ለመስራት በማያስችል የጤና ችግር ምክንያት ልጆችን ለመንከባከብና ለማሳደግ የማይችል ወላጅ ጋር የሚኖር ሕፃን ከሆነ፣
6) ሕፃኑ ምንም ድጋፍ አድራጊ አካል የሌለውና በአስቸኳይ የድጋፍ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከሆነ፣
7) ለችግር ተጋላጭ የሆነና የማይድን በሽታ ታማሚ ሕፃን ከሆነ፣
8) በሕፃናት የሚመሩ ቤተሰብ ጋር ያሉ ሕፃናት ከሆነ ፣
9) ምንም ገቢ ወይም ጧሪ በሌላቸው አረጋውያን የሚተዳደሩ ሕፃናት ከሆኑ፣
10) ለችግር የተጋለጠና አካል ጉዳተኛ ሕፃን ከሆነ፡፡

11. <u>ለሕፃናቱ የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ እና አስተዳደር ሁኔታ</u>

1. ከቤተሰባቸው ጋር የሚገኙ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ቁጥር አንድ ከሆነ ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ፣ ሁለት ከሆኑ ብር 1500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) እና ሶስት እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ ይሆናል፡፡
2. የሚሰበሰበው ወርኃዊ ገንዘብ በመስሪያ ቤቱ ሕጋዊ የሒሳብ ቋት ወይም ለዚህ ተግባር ተብሎ በፋይናንስ ቢሮ እውቅና እና ፈቃድ በሚከፈት የባንክ ሒሳብ ቁጥር የሚቀመጥ ይሆናል፡፡
3. የሚሰበሰበው ገንዘብ የሚቀመጥበት ሕጋዊ የባንክ አካውንት በተቋማቱ ቼክ ፈራሚዎች ወይም በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሕጋዊ ውክልና በተሰጠው ሠራተኛ አማካይነት የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡
4. ከሠራተኞች የሚሰበሰበው ወርኃዊ የአንድ መቶኛ መዋጮ ከደመወዛቸው በፔሮል የሚቆረጥ ሲሆን አፈጻጸሙ በየተቋማቱ ገንዘብ የሂሳብ ባለሙያዎች አማካይነት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. የድጋፍ ገንዘቡ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘረው መጠን ውጪ የሕፃናትን ችግር ውስጥ መሆን ከግምት ውስጥ ያስገባ በእናት አምባሳደሮች በዳሰሳ ጥናት ቀርቦ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ልዩ ትእዛዝ ካልተሰጠበት በስተቀር ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይም ይሁን በታች ክፍያ መፈጸም አይቻልም፡፡

12. <u>ስለድጋፉ ቀጣይነት</u>

1. የድጋፉ ተጠቃሚ እድሜ ከ18 ዓመት በላይ ሆኖ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግባት ካልቻለ፣ በኮሌጅ ወይም በቴክኒክና ሙያ ወይም የአጭር ጊዜ የሙያ ትምህርት እንዲሰለጥን በማድረግ በገቢ ማስገኛ ድጋፍ ማእቀፍ እንዲካተትና ራሱን እንዲችል ይደረጋል፤
2. የድጋፉ ተጠቃሚዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመግባት እድል ካገኙ ከሚማሩበት የትምህርት ተቋም በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ ድጋፉ የሚቀጥል ይሆናል፤
3. ለሕፃኑ ድጋፍ አድራጊ ድርጅት ከሚሰጠው አገልግሎት ውጪ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ ሕፃኑን ወደ ሌላ ድርጅት በመላክ ሌሎች ተጨማሪ

ድጋፎችን ማለትም የሕክምና ድጋፍ፣ ነፃ የትምህርት እድል፣ የሙያ ሥልጠና፣ የሥራ እድል ትስስር፣ እና የመሳሰሉትን ድጋፎች እንዲያገኝ ይመቻችለታል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሕፃናት ማሳደጊያና ማቋቋሚያ ተቋም አሰራርና ድጋፍ አገልግሎት

### 13. የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሚት ሕፃናትን ለመቀበል የሚያስፈልጋቸው ፈቃደኝነት እና ዝግጅት

የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሚት ሕፃናትን ለመቀበል የሚከተሉትን ፈቃደኝነት እና ዝግጅትን ሲያሟሉ ሕፃናትን ለማሳደግ ብቁ ናቸው፡-

1. በሌሎች የሕፃናት ድጋፍና ክብካቤ አማራጭ ዘዴዎች መደገፍ ያልቻሉ ሕፃናትን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ወይም የተቋም አገልግሎት የመጨረሻ አማራጭ የሕፃናት እንክብካቤ መሆኑን በማረጋገጥ ኃላፊነቱንና ሚናውን መወጣት የሚችል፣
2. አላማቸው ለሕፃናት መብትና ጥቅም በማስቀደም አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ፤
3. ለአካል ጉዳተኞች፣ ኤች.አይ. ቪ. በደማቸው ለሚገኝ እና ጥቃት ለደረሰሳቸው ሕፃናት የተለየ ድጋፍና እንክብካቤ ቅድሚያ ሰጥተው ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ፤
4. የሕፃናት ማሳደጊያው ስም ተግባሩን የሚገልጽና በማህበረሰቡ ጥሩ ትርጓሜ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
5. ተቋሙ የራሱ የሆነ ህፃናቱንና ሰራተኞችን የሚገዛ የመተዳደሪያ ደንብ ሊኖረው ይገባል፤
6. የሕጻናት ማሳደጊ ተቋሙ ድርጅቱን የሚገልጽ ታፔላ በሚታይና ግልጽ በሆነ ቦታ የሚለጠፍና የስልክ፣ ፖስታ፣ ኢሜልና የሚገኝበት ከተማ፣ ክ/ከተማ፣ ወረዳ እና ልዩ ቦታ ተጠቅሶ ግልጽ የሆነ አድራሻ ሊኖረው ይገባል፤
7. የሕፃናት ማሳደጊያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከቢሮው ጋር የሥራ ስምምነት ሊኖራቸው ይገባል፤

8. የሕፃናት ማሳደጊያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበር ከነበሩበት ቦታ የአድራሻ ለውጥ በሚያደርግበት ጊዜ አስቀድሞ ለቢሮ በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታቸውን ለመወጣት ዝግጁ የሆኑ፤
9. በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሕፃናት በተቋሙ የመቀበል አቅም፣ ከበጀት እና ከሰው ኃይል ቁጥር ጋር መመጣጠን አለበት፤

14. <u>በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም ውስጥ የሚያድጉ ሕፃናት</u>

1. ከውልደት እስከ 18 ዓመት የእድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት የተቋም አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ ከ18 ዓመት በላይ ቢሆኑም የተለያየ የቀለም ትምህርትና የሙያ ስልጠናዎችን በመከታተል ላይ ያሉ ታዳጊዎች ትምርታቸውን ወይም ስልጠናቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በተቋም ውስጥ አገልግሎቱን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
2. በሕጻናት ማሳደጊያዎች ውስጥ ሕፃናቱን በሚመለከቱ በማናቸውም ውሳኔዎች ላይ ሕፃናቱን ማሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡

15. <u>የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም ግዴታዎች</u>

1. ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከተቋጥሮ ዘመዶቻቸው ጋር ተቀላቅለው የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
2. ሕፃናት ፍቃደኛና ብቁ በሆኑ የአደራ ቤተሰቦች ድጋፍ እያገኙ የሚያድጉበት ሁኔታ ማመቻቸት፤
3. በቤተሰቦቻቸውና በወላጆቻቸው ሊያድጉ ያልቻሉትን ሕፃናት በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
4. ታዳጊዎች ከማህበረሰቡ ተዋህደው የራሳቸውን አቅም ፈጥረው ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ፤
5. ታዳጊዎች ከተቋም ውጭ በቡድን ቤት የሚያድጉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
6. ሕፃናት ወደ ተቋሙ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ ማጣራት ስራ መስራት፤
7. የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሙ አዲስ ሕጻናትን በሚቀበልበት ጊዜም ሆነ ከተቀበለም በኋላ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በሕፃናቱ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ያለመፍጠር፤
8. ተቋሙ ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ጥንቃቄ ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

9. ተቋሙ ሕፃናትን ሲቀበል በተቋሙ ውስጥ እንክብካቤ የሚያገኙ ሕፃናትን ማስረጃ በተገቢው መንገድ መያዝ፤

10. ከህፃናቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች ቢያንስ በ6 ወር አንድ ጊዜ የጤና ምርመራ ማድረግ፤

11. ተከታታይ የሆነ የሥነ-ልቦና የህክምና ድጋፍን ጨምሮ የኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ላሉ ሕፃናት አንቲ ሪትሮቫይራል መድሀኒትና ሌሎችም ተዛማጅ ህክምናዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፤

12. በተቋሙ ውስጥ የሚያድጉ ሕፃናት የማህበረሰቡን ወግ፤ እሴት፤ ባህል በራስ መተማመን እንዲፈጥሩ ማድረግ፤

13. ሕፃናት ማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ትምህርት ቤቶች ወይም ከማህበረሰቡ ልጆች ጋር እንዲማሩ ማድረግ፤

14. በእረፍት ጊዜያቸው ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች በሚመዘግቡበት ወቅት ወደ ቤተሰብ፤ ዘመድ፤ ጓደኞችና ጎረቤቶች ዘንድ ሄደው እንዲያሳልፉ መፍቀድ፤

15. በእረፍት ጊዜያቸው በሕፃናቱ ፍላጎት መሰረት ቤተሰብ፤ ዘመድ፤ ጓደኞቻቸውና ጎረቤቶች መጥተው ሕፃናትን እንዲጠይቋቸው መፍቀድ፤

16. በተቋሙ ውስጥ የተለያዩ ክለቦች ሙዚቃዎች፤ ድራማዎች ሥዕልና እንዲያቋቁሙ ማድረግና የተለያዩ ሥራዎችን ለማህበረሰቡ አባላት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

17. በዓላትን ከማህበረሰቡ ወይም ከዘመዶቻቸው ጋር እንዲያከብሩ ማድረግ፤

18. ለሕፃናት ተሞክሯቸውን እንዲያካፍሉ የታወቁ የማህበረሰቡን አባላት መጋበዝና የህይወት ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ፤

19. በተቋማቱ ውስጥና ውጭ ማህበረሰቡን ያሳተፉ የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችን ማካሄድ፤

20. እንደ ህፃናቱ እድሜና የግንዛቤ ደረጃ በማሳደጊያዎች ውስጥ እነርሱን በሚመለከት ውሳኔ ህፃናቱን ማሳተፍ፤

21. ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በተለያዩ የልማት ስራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንዲሁም ሌሎች የበጎ ፍቃድ ተግባራት ላይ እንዲሰማራ ማድረግ፡፡

22. ቢሮው ሳያውቀው በከተማ ውስጥ በየትኛውም አይነትና ሁኔታ ሕፃናትን በአንድ ቦታ ሰብስቦ ማሳደግም ሆነ የሕጻናት ማሳደጊያ አቋቁሞ መስራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

16. <u>ሕፃናት ወደ ተቋሙ የሚገቡበት ሁኔታ</u>

1. ሁለቱንም ወላጆች በህይወት የሌሉ ከሆነ፤
2. በህይወት ያለው ወላጅ ፃኑን ለማሳደግ ምንም ዓይነት አቅም የሌለው ከሆነ፤
3. ተጥሎ የተገኘ ሕፃን ከሆነ፤
4. ሕፃኑ ወላጅ ቢኖረውም ወላጆቹ የጤና ችግር ያለባቸው ወይም ስር የሰደደ በሽታ፣ ወይም የአልጋ ቁረኛ የሆኑና ሰርተው ሕፃኑን ማስተዳደር የማይችሉ ከሆነ፣
5. ጥቃት የደረሰበት ሕፃን ከሆነ፣
6. ልዩ ፍላጎት ያለው ሆኖ የሚደግፈው አካል ያጣ ከሆነ፣
7. ለጎዳና ህይወት ወይም ለተለየ አስገዳጅ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ ችግር ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ፤
8. በሌሎች የሕፃናት አማራጭ የክብካቤ አገልግሎት መረዳት ያልቻሉ ከሆነ፡፡

17. <u>ሕፃናት ወደ ተቋም ሲገቡ መያዝ የሚገባቸው መረጃዎች</u>

ሕፃን ወደ ተቋም እንዲገባ የሚወሰነው የሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና ፖሊስ መሆን ያለበት ሲሆን ሕፃኑ ወደ ተቋም ሲገባ የሚከተሉት መረጃዎች በሚገባ ተጣርቶ መያዝ አለበት፤

1. የሕፃኑ ሁኔታ ወይም የሕይወት ታሪክ የሚገልፅ ማስረጃ፤
2. የወላጆቹን ሁኔታ/የጤና፣ በሕይወት ስለመኖራቸው፣ የመጥፋት ውሳኔ ወዘተ/ የሚገልፅ ማስረጃ፤
3. የሕፃኑ የልደት ካርድ፤
4. የሕፃኑ ፎቶ ግራፍ ማስረጃ፤
5. በፖሊስ በኩል ለሚገቡ ሕጻናት ከሆኑ የፖሊስ ማስረጃ፤
6. ከማህበረሰብ የሚገባ ከሆነ የሚያስገባው አካል የሞግዚትነት ወይም የአሳዳጊነት ማስረጃ፣
7. ሕፃናት የተቋም አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ለቢሮው የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤና ለሕፃኑ ሌሎች አማራጮች ተፈልገው ያልተሳኩበትን ምክንያት ማስረጃ፤
8. በሚመለከተው የክፍለ ከተማ ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት የሕፃኑ የህይወት ታሪክና የቤተሰቦቹ ማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

18. <u>በተቋም ውስጥ ያሉ ሕጻናት መረጃ አያያዝ</u>

1. በተቋም ውስጥ ሕፃናት በትምህርት፣ በጤና፣ በማኅበራዊ፣ በስነ-ልቦናዊና በመንፈሰዊ ለውጣቸውን መመዝገብ የሚያስችል ለእያንዳንዱ ህጻን የራሱ የሆነ የግል ማህደር ሊኖረው ይገባል፤
2. እያንዳንዱ ለሕፃናቱ በተለያየ ጊዜ የተሰጡ የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት አይነቶች በሕፃናቱ መዝገብ ላይ ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ ተመዝግቦ መቆየት አለበት፤
3. በአንድ ሕፃን ማህደር ውስጥ የሕፃኑ ፎቶ ግራፍ፣ የክትባት ካርድ፣ የሕጻኑ የሕይወት ታሪክ የሚገልጹ አጠቃላይ መረጃዎች በተገቢ ሁኔታ ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል፤
4. ተቋሙ ውስጥ ያሉ ሕፃናት በሌላ አማራጭ የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት ማለትም /የጉዲፈቻ፣ የአደራ ቤተሰብ፣ የቡድን ቤት፣ ማቀላቀል፣ ማቋቋም፣ ወደ ሌላ ተቋም ማዘዋወር ወዘተ/ እንዲረዱ የተደረጉ ከሆነ አማራጩ ምን እንደሆነና የት እንደሚገኝ የሚገልፅ ከአማራጭ እንክብካቤው በኋላ ያለውን ሪፖርት የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

19. <u>የሕጻናት ማሳደጊያ ተቋም አገልግሎት</u>

አንድ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም በተቋም ውስጥ ለሚያድጉ ሕፃናት የሚከተሉትን መሰረታዊ አገልግሎቶች ይሰጣል፡-

1. መጠለያ፤
2. ምግብ፤
3. አልባሳት፤
4. ጤና /ፅዳትና ንፅህና/፤
5. ጨዋታና መዝናኛ፤
6. ሕፃናት በማህበረሰብ እንክብካቤ የሚረዱበትን ሁኔታ መፈለግ፤
7. ትምህርትና ስልጠና ያመቻቻል፣
8. ተከታታይነት ያለው የሥነ-ልቦና አገልግሎት፤
9. የሕፃናት ጥበቃ ፖሊሲ ማውጣትና መተግበር፤
10. የሕግ ድጋፍ ማመቻቸት፤
11. ቅንጅትና ትብብር መፍጠር፤

20. <u>ልዩ ፍላጎት ላሏቸው ሕፃናት ልዩ እንክብካቤ ስለመስጠት</u>

የሕጻናት ማሳደጊያ ተቋሙ ልዩ ድጋፍ ለሚያሳድጋቸው አካል ጉዳተኛ ሕፃናት የሚከተሉትን ልዩ እንክብካቤ ማድረግ ይኖርበታል፡-

1. ሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ ዊልቸር እና የመሳሰሉት፤
2. በሙያው የሰለጠነ የሰው ሀይል፤
3. የብሬል ስልጠናን፣ የምልክት ቋንቋ ስልጠናን፣ የመሳሰሉትን አገልግሎቶች እንዲሁም ተቋሙ በቅጥር ግቢ የሚገኙ ማንኛቸዉም አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
4. ለሕፃናት የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና
5. የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም የሚያሳድጓቸውን ሕፃናት ከመዋለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ የማስተማር ኃላፊነት አለበት፡፡
6. የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም ለሚያሳድጋቸው ሕፃናት አስፈላጊውን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ያቀርባል፡፡
7. ተቋሙ ከሚያሳድጋቸው ሕፃናት መካከል የትምህርት አቀባበል ላይ ችግር ላለባቸው ልዩ የትምህርት ድጋፍ ያደርጋል፡፡
8. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት የትምህርት እድል የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻት አለበት፡፡
9. ሕፃናቱ በትምህርት ላይ ስለሚያሳዩት ለውጥ የትምህርት ክትትል ባለሙያው በየጊዜው እየተከታተል ለተቋሙ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
10. ተቋሙ አግባብነት ያላቸው መጽሐፍት የሚገኙበት የንባብ ቤት /Library/ ሊኖረው ይገባል፡፡
11. ተቋሙ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተቋሙ ቅጥር ግቢ መክፈት አይጠበቅበትም ከከፈተ ግን ህፃናቱን እንዳይገለሉ በማድረግ ከማህበረሰቡ ልጆች ጋር አብረው የሚማሩበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡
12. ተቋሙ የሙያ ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ታደጊዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡
13. ታዳጊዎች በሙያ ስልጠና ብቁ የሚሆኑት ቢያንስ የሚከተሉትን ያሟሉ መሆን አለባቸው፡-

    ሀ) ዕድሜቸው ከ14 ዓመት በላይ የሆነ፤

    ለ) የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ፤

ሐ) የሙያ ትምህርት ለመማር ዝንባሌ ያላቸው፣

መ) የቀለም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ፍላጎት የሌላቸውና መቀጠል ያልቻሉ የሙያ ስልጠና የሚጠቅማቸው ከሆነ፤

14. ተቋሙ ለሚያሰለጥናቸው ታዳጊዎች ሙሉ ቁሳቁሶች፤ የስልጠና ክፍያ፤የምዝገባ ክፍያና የመጓጓዣ ወጪ መሚላት አለበት፤
15. ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለሚወስዱ ሰልጣኞች አስፈላጊውን ክፍያ ይፈጽማል፤
16. ተቋሙ ስልጠና ያጠናቀቁ ሕፃናት ከማህበረሰቡ ጋር ለመቀላቀልና ራሳቸውን ለመቻል በሚያደርጉት ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
17. በማንኛውም አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሕፃናት/ታዳጊዎች በተቋም ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አይፈቀድም፡፡

21. <u>በህፃናት ማሳደግያ ማዕከላት ላሉ ሕፃናት ስለሚደረግ ድጋፍ መስፈርቶች</u>

የትምህርት ድጋፍ ወጪ ተጠቃሚዎች የሚሆኑት ከዚህ የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. በተቋሙ ውስጥ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ ቅድመ መደበኛ፣1ኛ ደረጃ፣2ኛ ደረጃ እና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው በመከታተል ላይ የሚገኙ ሊሆን ይገባል፤
2. በመደበኛ ትምህርት፣በከፍተኛ የትምህርት ተቋም፣ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ትምህርታቸውን ወይም ስልጠናቸውን እየተከተራተሉ ያሉ መሆን አለባቸው፣፤
3. ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ወይም በቀድሞው መሰነዶ ትምህርት በኋላ በኮሌጅ፣ በቴክኒክና ሙያ ለትምህርትና ሥልጠና የገቡ እና የብቃት ማረጋገጫ /COC/ ፈተና ለሚወስዱ፤
4. በቅድመ መደበኛ፤ አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ፤
5. የሚኒስትሪ እና የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ወይም የማትሪክ ፈተና ለሚወስዱ፤
6. ወደ ኮሌጅ ወይም ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መግባት ያልቻሉ እና ፍላጎት የሌላቸው የቀለም ትምህርት መቀጠል ያልቻሉ ወይም ፍላጎት የሌላቸው እና የተለያዩ አጫጭርና ረዥም የሙያ ሥልጠናዎችን የሚከታተሉ ተማሪዎች፤

7. በትምህርት አቀባበላቸው ችግር ያለባቸውና ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እንደሚያስፈልጋቸው የሚማሩበት ትምህርት ቤት አስተያየት የተሰጣቸው ተማሪዎች፤
8. የተለያዩ አሳይመንቶችን እንዲሰሩ ከትምህርት ቤት ሲታዘዙ የተቋሙ የትምህርት ክትትል ክፍል ሲያረጋግጥ እና አስፈላጊነቱ ሲታመንበት፤
9. ትምህርት ቤቱ የሚያዘጋጃቸው የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ከትምህርት ቤቱ የተጠየቀ ሲሆን፤
10. በትምርት ቤቶች የሚደረጉ የተለያዩ ትምህርታዊ ጉዞዎች ሲዘጋጁ ትምህርት ቤቶች የሚጠይቃቸው ክፍያዎች፤
11. በትምህርት ቤቶች የሚጠይቁ የተለያዩ የልማትና የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ ወጪዎች፣ ለፎቶ ግራፍ፣ ለመታወቂያ፣ለማስጠረዝ፣ለህትመት፣ፎቶ ኮፒ፣ ሲጠየቁ መረጃ ሲቀርብ፤
12. የተለያዩ የስፖርት መርጃ መሳሪዎችና ትጥቆች እንዲገዙ ሲጠየቁና አስፈላጊነቱ ሲታመኑበት፡፡
13. ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግባት ሳይችሉ ቀርተው በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብተው በመማር ወይም በመሰልጠን ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው፤
14. ከአጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (12ኛ ክፍል) በኋላ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ቢመጣላቸውም በራሳቸው ፈቃድ ወደ ሙያ ትምህርት ገብተው በመማር ላይ ያሉ፤
15. የትምህርት ድጋፍ ወጪ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ተቋሙ የማረጋገጫ ማስረጃ እና የወጪ መጠየቂያ ደብዳቤ ለቢሮ ማቅረብ አለባቸው፡፡ከ

22. <u>የከፍተኛ ትምህርት ወይም ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መርሃ-ግብር</u>

በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመንግስት ለተመደቡ ተማሪዎች፡-

1. የመጀመሪያ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ለሚገቡ ታዳጊዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚያስገባ ነጥብ ስለማምጣታቸው ማስረጃቸው ሲቀርብ እና ትምህርታቸውንም እንደሚከታተሉ በተቋሙ ተረጋገጠ በሚመጣው ደብዳቤ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ ይህም ሲባል ተማሪው ገና ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

/የትምህርትና የመኝታ ቁሳቁሶች፣ የስፖርት ትጥቆች፣ ቦርሳ፣ የልብስ ሻንጣ፣ ብርድ ልብስ፣ አንሶላና የትራስ ጨርቅ ወይም ለአንድ ጊዜ ብቻ ግዥ ተፈጽሞ ይሰጣል፡፡

2. አዲስ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ተቋሙ በሚያቀርበው ማረጋገጫ መነሻነት የኪስ ገንዘብ በየወሩ 2000.00 (ሁለት ሺህ ብር ) የሚሰጥ ሲሆን ይህም የግማሽ መንፈቅ ዓመት ተሰልቶ አንዴ በባንክ የሚላክ ይሆናል፡፡
3. ከአንደኛ ዓመት በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ስለቀጣይነታቸው ከሚማሩበት ተቋም በሚያመጡት ማስረጃ መሠረት ከላይ የተገለጸው ገንዘብ በየሰሚስቴሩ የሚላክ ይሆናል፤ ይህም በየዓመቱ በትምህርት ላይ የሚቆዩበትን አስር ወራት ብቻ ታሳቢ ያረገ ይሆናል፤
4. ተማሪው ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲገባና ትምህርቱን ጨርሶ ለእረፍት ሲመለስ እንደ የአካባቢው ርቀት ታሪፍ የደርሶ መልስ ትራንስፖርት መጓጓዣ ገንዘብ የሚሰጥ ይሆናል፤
5. በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ኮሌጆች፣ የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ውስጥ ለሚሠለጥኑ ተማሪዎች የኪስ ገንዘብ የወሩ 800.00 (ስምንት መቶ ብር) ሲሆን ይህም የግማሽ መንፈቅ ዓመት ተሰልቶ አንዴ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የትራንስፖርት ወጪያቸው የደርሶ መልስ መጓጓዣቸው እንደ የቦታው ርቀት ተሰልቶ በየወሩ የሚሰጥ ሲሆን ይህም በዓመት ውስጥ ትምህርት የሚሰጥበትን ወቅት ብቻ ታሳቢ በማድረግ ተስልቶ የሚሰጥ ይሆናል፤
6. ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ለሚመረቁ ተማሪዎች የመመረቂያ ብር 12,000.00 (አስራ ሁለት ሺህ ብር) ይሰጣል፤
7. ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመመረቂያ ጽሁፍ ወጪ የሚሆን ገብዘብ ወጪ 4,000.00 /አራት ሺህ ብር/ የሚሰጥ ይሆናል፤
8. ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዲፕሎማ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ለሚመረቁ ተማሪዎች የመመረቂያ ሙሉ ወጪ (የመመረቂያ አልባሳት ማለትም ሙሉ ሱፍ፣ ጫማ፣ ሸሚዝ፣ ከራባት፣) 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ይሰጣል፤
9. ወደ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎች በበጀት ዓመት ተፈቀደላቸውን የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ከተቋሙ ይዘው እንዲሄዱ ይደረጋል፤

10. ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለገቡ ተማሪዎች የአልባሳት ወጪ ከተቋማቸው በአልባሳት ኖርም መሠረት ወጪ ተደርጎ በየዓመቱ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤ ይህ መርሃ ግብር ታዳጊዎች ራሳቸውን ችለው ሲቋቋሙ እና ተቋሙን ሲለቁ ብቻ የሚቋረጥ ይሆናል፤
11. በትምህርት ወይም ሥልጠና ላይ ለልምምድ ለሚወጡ የከፍተኛ ትምህርት ታዳጊዎች ለልምምዱ የሚሆን ወጪ የሚሸፈነው የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ስለጉዳዩ በጻፈው ደብዳቤ መሠረት የሚስተናገድ ሆኖ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ በቢሮው ሲረጋገጥ እና ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፡፡

23. <u>በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለሚከታተሉ የትምህርት ድጋፍ ወጪ</u>

1. በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለሚከታተሉ ታዳጊ ተማሪዎች በተቋሙ በተረጋገጠ ማስረጃ መሠረት የትምህርት ድጋፍ ወጪ ሲጠየቅ የኪስ ገንዘብ 400 (አራት መቶ ብር ብቻ) ይሰጣቸዋል፤
2. ሙያዊ ልዩ ሥልጠና እየተከታተሉ ለሚገኙ ታዳጊ ተማሪዎች በተቋሙ በተረጋገጠ ማስረጃ መሠረት የትምህርት ድጋፍ ወጪ ሲጠየቅ የኪስ ገንዘብ 200 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) እንዲከፈላቸው ይደረጋል፤
3. በማሠልጠኛ ተቋሙ ለሙያ ሥልጠናው የሚያግዙ ግብአቶች እንዲሟሉ ሲጠየቅ አስፈላጊ ግብአቶች እንዲሟሉ የሚደረግ ይሆናል፤
4. የብሔራዊ ፈተና ተፈትነው ውጤት ሳይመጣላቸው በመቅረቱ ወይም መደበኛ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ የቴክኒክና ሙያ ት/ቤት ወይም የኮሌጅ ወይም የሙያ ስልጠናዎችን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ትምህርታውን መከታተል ያለባቸው በመንግስት ተቋማት ውስጥ ብቻ ሲሆን ለዚህም አስፈላጊውን የትምህርት ወጪ የሚቀርቡ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

24. <u>የትራንስፖርት፣ የምሳ እና በትምህርት ቤት የሚጠየቁ ወጪዎች</u>

1. በከተማዋ ቅድመ መደበኛ፣ አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ፤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤት፤ ቴክኒክና ሙያ፣ ልዩ የሥልጠና ማዕከላት፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በመመላለስ ለሚማሩ ሕፃናትና ታዳጊዎች የትራንስፖርት ወጪ በወቅቱ በከተማዋ በሚኖረው ታሪፍ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡
2. ለ6ኛ ወይም 8ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና እና 12ኛ ክፍል ብሔራዊ (ማትሪክ) ተፈታኞች በወቅቱ በሚመደቡበት የመፈተኛ ጣቢያን መሠረት ባደረገ ከማሳደጊያ

ተቋሙ ርቀቱ በተሰላ መልኩ እና ተቋሙ በሚልከው መረጃ መሠረት ምሳን ጨምሮ የትራንስፖርት ወጪያቸው የሚከፈል ይሆናል፡፡ የምሳ ወጪ ክፍያ ለሁሉም ተፈታኝ ሳይሆን ከተቋም እንደ መፈተኛ ጣቢያ ርቀት ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3. በት/ቤት ለተጠየቀ ለትምህርታዊ ልምምድ /አፓረንትሺፕ/፣ ለብቃት ማረጋገጫ ምዘና /COC/ በትምህርት ቤት ለሚካሔዱ ትምህርታዊ ጉዞዎች /አገርህን ዕወቅ/፣ ት/ቤቶች ለልማት የሚጠይቁአቸው ወጪዎች ሲኖሩ ት/ቤቶች በሚልኳዋቸው መረጃዎች መሠረት ወጪዎች የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡
4. ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች ወይም ለትምህርት፣ ለፈተና፣ ለልምምድ እና ጉዞዎች የአካል ጉዳት ኖሮባቸው በረዳት ለሚንቀሳቀሱ ተማሪዎች የትራንስፖርት እና የምሳ ወጪያቸው ረዳታቸውን ስለሚጨምር በእጥፍ ይሆናል፡፡
5. ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የፎቶ ግራፍ መነሻ፣ የአሳይመንት መሥሪያ፣ በዓይነት እንዲቀርቡ የታዘዙ ቁሳቁሶች ሲኖሩ ትምህርት ቤቱ በላከው መረጃ መሠረት ተገናዝቦ ወጪው በገንዘብ እና እንደ አስፈላጊነቱ በቁሳቁስ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

25. <u>የአልባሳት ድጋፍ ወጪ ማስፈጸሚያ</u>

1. በራሳቸው አልባሳት መግዛት የማይችሉ እና በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ሕፃናት ማቆያና ተሃድሶ ማዕከል ውስጥ ያሉ ሕፃናት የአልባሳት አቅርቦት በየተቋማቱ ጥያቄ መሠረት በቢሮ ግዢ እንዲቀርብ የቢሮ ኃላፊ ውሳኔ ሲሰጥበት ተፈፃሚ ይሆናል፡
2. የአዲስ አበባ ወንድ እና የአዲስ አበባ ሴት ታዳጊዎች ከማኅበረሰቡ ልጆች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ በመሆናቸው ልብስ በራሳቸው እንዲገዙ የሚፈቀድላቸው ሲሆን
   ሀ) ዕድሜያቸው ከ8 እስከ 18 ዓመት ለሆኑ ለአዲስ አበባ ወንድ እና ለአዲስ አበባ ሴት ሕፃናት ማሳደጊያና ማቋቋሚያ ማዕከላት ውስጥ ለሚገኙ ታዳጊዎች የአልባሳት በጀት በዓመት 8,000.00 (ስምንት ሺህ ብር ብቻ) የሚሰጥ ይሆናል ይሆናል፤
   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ብር 8,000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ለሕፃናት በአመት በሁለት ዙር የሚሰጣቸው ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ክፍያ በመስከረም ወር ብር 4000.00 (ዐራት ሺህ ብር) እንዲሁም የሁለተኛው ዙር

ደግሞ በየካቲት ወር ብር 4000.00 (ዐራት ሺህ ብር) የሚሰጣቸው ሲሆን ለአልባሳት መግዣነት ብቻ የሚውል ይሆናል፤

ሐ) የአልባሳት ግዥ አፈፃፀም እንደየዕድሜያቸው፣ በፍላጎታቸውና ምርጫቸው በተቋሙ ኃላፊ በኩል በሚመደቡ /በሚወከሉ/ ተንከባካቢ ሠራተኞች /ሞግዚቶች/ በኩል ተፈፃሚ ይሆናል፤

መ) አዲስ ወደ ተቋሙ የገባ እና ከ3 ወር በላይ በተቋሙ የቆየ ሕፃን ወይም ታዳጊ ወደ ቤተሰቡ መቀላቀል የማይችል ሆኖ ሲገኝ ከተቋሙ በሚቀርበው መረጃ መሠረት የግማሽ ዓመቱን በጀት ወይም ብር 4000.00 (ዐራት ሺህ ብር ብቻ) የሚሰጠው ይሆናል፤

ሠ) ተቋሙ ውስጥ የቆይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ማለትም ወደ ቤተሰቦቻቸው የተቀላቀሉ ወይም የተቋቋሙ ሕፃናት ከተቋቋሙበት /ከተዋሃዱበት/ ጊዜ ጀምሮ የተቋም አገልግሎት የሚቋረጥ በመሆኑ የአልብስ በጀት ተጠቃሚ አይሆኑም፤

ረ) ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ሆኗቸው በዩኒቨርሲቲ፣ በኮሌጅ እና በሙያ የሥልጠና ተቋማት በመማርላይ ያሉ ታዳጊዎች ትምህርታቸውን አለማጠናቀቃቸውን በተቋሙ ከተረጋገጠ በዚህ መመሪያ ላይ የተወሰነውን የአልባሳት በጀት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

3. ከቢሮው ጋር የፕሮጀክት ውል ስምምነት ፈጽመው የሕፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት ለሚሰጡ ማዕከላት በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ በተቀመጠው የሕፃናት ዕድሜ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፣

26. <u>ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች</u>

ከትምህርት ጋር በተያያዠ ሌሎች ወጪዎች አስፈላጊነታው በተቋሙ ተረጋግጦ ከተጠቃሚ ታዳጊዎቹ ዝርዝር ጋር ተያይዞ በደብዳቤ ለቢሮ ሲቀርቡ እንደሚከተለው የሚፈቀድ ይሆናል፡-

1. የፕሮጀክት፣ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ለሚጠየቁ የትምህርት ቁሳቁስ (ማስመሪያ፣ ቻርት ወረቀት፣ የግራፍ ወረቀት፣ ቲ ስኩዌር፣ የደህንነት ጫማ፣ አንጸባራቂ ልብስ፣ ኬፕ) ተቋሙ በሚያቀርበው ማረጋገጫ መሠረት፤
2. ልዩ ልዩ የትምህርት ቤት የልማት ክፍያዎች፤

3. ከትምህርት ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶች ለተለያዩ አገልግሎቶች ለተማሪዎች ፎቶ መነሻ፤
4. ታዳጊዎች ትምህርታቸውን ለመከታተል የማያስችል ችግር ገጥሞ ተማሪዎች የግድ በቤታቸው ውስጥ ሆነው ትምህርታቸውን መከታተል ሲኖርባቸውና የመማሪያ መጻሕፍት ወይም ማስታወሻ ኖቶች በኢንተርኔት የሚለቀቁ ሆኖ ትምህርትን ለመከታተል ያስችል ዘንድ ሁኔታው ታይቶ በቢሮ እንዲመቻች ይደረጋል፤
5. የፀጉር መሰሪያ ክፍያ ከተቋሙ በሚቀርበው ፍላጎት መሰረት የሚስተናገድ ሲሆን ለወንድ ታዳጊዎች በወር ብር 100 (አንድ መቶ ብር) እና ለሴት ታዳጊዎች በወር ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) የሚከፈል ይሆናል፤

27. <u>የቢሮ፣ የተቋማት፣ የአሳዳጊዎች እና የታዳጊዎች ሚና</u>

1. የቢሮው ሚና፡-
   ሀ) ለሕፃናት ወጪ ተደርጎ የተሰጠው የአልባሳት በጀት በአግባቡ ለሕፃናት መድረሱን ክትትል በማድረግ መመሪያውም ተጥሶ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
   ለ) ለሕፃናት የተመደበው የአልባሳት በጀት ወጪ በቂ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ወቅታዊ የገበያ ጥናት በማድረግ ማስተካከያ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡
   ሐ) የሕጻናት አልባሳትግዥ የሕፃናትን ፍላጎትና እርካታን ያማከለ ስለመሆኑ፣ ታዳጊዎች በቂ የገንዘብ አጠቃቀም ክህሎት ስለመኖራቸው፣ ገንዘባቸውን በተገቢ ሁኔታ ስለመጠቀማቸውን ቼክ-ሊስት በማዘጋጀት ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
2. የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ሚና፡-
   ሀ) ለአልባሳት የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
   ለ) አዳዲስ ሕፃናት ወደ ተቋሙ በሚገቡበት ወቅት መረጃቸውን በአግባቡ በማጣራት ወደ ቤተሰቦቻቸው ማቀላቀል የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የአልባሳት በጀት ጥያቄ አደራጅቶ ያቀርባል፤
   ሐ) በየዓመቱ የአልባሳት በጀት በሚጠየቅበት ወቅት የአልባሳት ወጪ የሚያስፈልጋቸውንና የማያስፈልጋቸውን ታዳጊዎች ለይቶ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤

መ) በየተቋማቱ የተመደቡ የሞግዚት ሠራተኞች ለሕፃናት ወጪ የሚደረገውን ገንዘብ በየስማቸው እየፈረሙ መረከብ ይኖርባቸዋል፤

ሠ) ሞግዚቶች የተረከቡት ገንዘብ ለአልባሳት ግዥ ብቻ ማዋላቸውን ክትትል ደርጋል ይቆጣጠራል፣ ችግር ሲያጋጥም አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ይወስዳል ለቢሮ ሳውቃል፤

ረ) ማንኛውም ታዳጊ ተቋሙን ሳያሳውቅ በገዛ ፍቃዱ ተቋሙን ሲለቅ፣ በድሲፕሊን ተቀጥቶ በወንጀል ተከሶ ተጠያቂ ሲሆንና ከተቋሙ ውጪ ከ15 ቀን በላይ በሚቆይበት ጊዜ የአልባሳት በጀት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን የማይችል መሆኑን በወቅቱ ለቢሮ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

28. <u>የተንከባካቢዎች ወይም የሞግዚቶች ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1. በተቋሙ በኩል ለሕፃናቱ አልባሳት ግዥ ለማስፈጸም የተመደበ ማንኛውም ተንከባካቢ ሠራተኛ ወይም ሞግዚት ጥራቱን የጠበቀ እና አግባብነት ያለው ልብስ እንዲገዛ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፤
2. ሕፃናት የአልባሳት በጀትን በአልባሌ ነገሮች ላይ እንዳያውሉ መምከር፣ የማስተማር፣ የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና ከአቅም በላይ ከሆነ ለተቋሙ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

29. <u>የታዳጊዎች ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1. የሚሰጣቸውን የአልባሳት በጀት በአግባቡ ለልብስ ብቻ የመጠቀም ኃላፊነት አለባቸው፤
2. በየተቋሙ የተቋቋሙ የታዳጊ ኮሚቴዎች የጓደኞቻቸውን ፍላጎት በመገንዘብ አልባሳት ሲገዛ አብሮ ማጋዛት ማስተባበርና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤
3. በአልባሳት በጀት ላይ ችግር ወይም ቅሬታ ቢፈጠር በታዳጊዎች ተወካይ አማካኝነት ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል፡፡ የቀረበው ቅሬታ አግባብ መሆኑን በማጤን ቢሮው ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፤
4. በመመሪያ መሠረት ገንዘቡን ላልተፈቀዱ ነገሮችን ማዋል በዲስፕሊን የሚያስጠይቅ ሲሆን እንደ ጥፋቱ ደረጃ ከአንድ ግምሽ በጀት ዓመት ጥቅምን ማጣት እስከ ከተቋም መሰናበት የሚደርስ ቅጣት ሊያስቀጣ ይችላል፡፡

30. <u>ሕፃናትን ወደ ቤተሰብ የሚያቀላቅሉ የህፃናት ማሳደጊያ ማዕከላት ግዴታዎች</u>

1. ከአዲስ አበባ ክልል ውጪ ሲሆን
   ሀ) ሕፃናት ከተቋማት ወጥተው ትራንስፖርት እስከሚሳፈሩበት አውቶቡስ ተራ ድረስ የሚያደርስ ትራንስፖርት በተቋሙ በኩል የሚመቻች ይሆናል፤
   ለ) የታዳጊ የቀን ወጪ ለምግብና መኝታ የወቅቱን ሁኔታ ያገናዘበ ሆኖ ከ400.00 (አራት መቶ ብር) ጀምሮ እንደ የቦታው ርቀትና ቆይታተሰልቶ በሚዘጋጀው መሠረት ይሆናል፤
   ሐ) የመጓጓዣ ዋጋ ወጪ በወቅቱ ታሪፉ መሠረት የሚሸፈን ይሆናል፤
   መ) የባለሙያ አበል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ቢሮ ባወጣው የአበል ወጪ መመሪያ መሠረት ሆኖ የባለሙያውን የቆይታ ጊዜን እና ከዋናው መንገድ ተጨማሪ የጉዞ ርቀትን ያገናዘበ ይሆናል፡፡

2. አዲስ አበባ ክልል ውስጥ ሲሆን

ሀ) የክፍለ ከተማ ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የሕጻኑን ቤተሰብ በተያዘው ዝርዝር መረጃ መሠረት የቤተሰቡን አድራሻ ያፈላልጋል፤

ለ) ሕፃኑን ቤተሰቦቹ ወደሚኖሩበት አድራሻ ድረስ በቢሮው ወይም በማሳደጊያ ተቋሙ ትራንስፖርት አቅርቦት እንዲቀላቀል ይደረጋል፤

ሐ) ለዚህ አገልግሎት የተመደበው መኪና ወጪ መሸፈኛ ከተበጀተለት የነዳጅ በጀት በተጨማሪ ለቅልቅል የሄደበት ርቀት በኪሎ ሜትር ተሠርቶ እንዲሸፈን ይደረጋል፤

መ) ሕፃናቱን ወደ ቤተሰቦቻቸው የማቀላቀሉ ሥራ በክፍለ ከተማ ደረጃ በሚሆንበት ጊዜ የማቀላቀል ሂደቱ በክፍለ ከተማ ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት በኩል የሚፈጸም ይሆናል፡፡

31. <u>ሕፃኑን ከወላጆቹ ወይም ከተቋጥሮ ቤተሰብ ጋር ስለማቀላቀል</u>

1. ሕፃኑ ወይም ታዳጊው ወደ ቤተሰቡ ስለመቀላቀሉ ከሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ፣ ከፖሊስ፣ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት እና የማኅበራት ተወካይ ታዛቢ እና አረካካቢ ሆነው ባሉበት የርክክቡ ሥነ-ሥርዓቱ ይካሄዳል፤
2. ሕጻኑን ከቤተሰብ ወይም አሳዳጊ ጋር ለማቀላቀል የወሰደው አካልወይም ባለሙያው ሕጻኑን በተገቢው ሁኔታ ስለማቀላቀሉ የፎቶ ግራፍ መረጃን ጨምሮ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ሕጋዊ ማስረጃ ለቢሮው ማቅረብ ይጠበቅበታል፤ ሆኖም ግን ሕጻኑን ከቤተሰብ ጋር የማቀላቀሉ ሂደቱ ላይ ልዩ እክል በሚገጥምበት ጊዜ ባለሙያዊ ሕጻኑን ቀድሞ ወደሚኖርበት ተቋም የመመለስ ኃላፊነት አለበት፤
3. ሕጻኑን የሚያቀላቅለው ባለሙያ የሕጻኑን ፆታ መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ፆታ የሚያቀላቅሉበትን ሁኔታ ተቋሙ ሊያመቻች ይገባል፤
4. ሕጻኑ/ታዳጊው ወደ ቤተሰቡ በሚቀላቀልበት ጊዜ ስለሚደረግለት አስፈላጊ ድጋፍ የሕጻናትን ጉዳይ የሚመለከተው የክልሉ መንግስት አካል ኃላፊነት ይሆናል፤
5. አግባባዊ የሆነ የማቀላቀል ሂደትን ተከትሎ የተቀላቀለ ሕፃን ወይም ታዳጊ በምንም ዓይነት ሁኔታ ዳግመኛ ወደ ተቋም ተመልሶ እንዲኖር አይፈቀድም፤
6. ከቢሮ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያላቸው የማቀላቀል ስራ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሪፖርት ለቢሮው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

32. <u>በአዲስ አበባ ውስጥ ለተቀላቀሉ ሕፃናት የድህረ ቅልቅል ክትትል ስርዓት</u>

1. የወረዳ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤቶች በየወረዳዎቻቸው የተቀላቀሉ ሕፃናትን በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ ለክፍለ ከተሞቻቸው ሪፖርት ያደርጋሉ፤
2. ክፍለ ከተሞች በየወረዳዎቻቸው የተቀላቀሉ ሕፃናትን በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ እና በመጠመር ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋሉ፤
3. ሕፃናትን የተረከቡ ቤተሰቦችን በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የማቋቋም ስራን በሚመለከት ቢሮው ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት የማስተሳሰር ሥራ ይሠራል፤
4. ቢሮው በከተማው ወደ ቤተሰብ መልሰው የተቀላቀሉ ሕፃናትንና ቤተሰቦቻቸውን በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ቤቶቻቸው ወርዶ ክትትል ያደርጋል፤
5. የተቀላቀለው ሕፃን ወይም ታዳጊ ዕድሜው 18 ሲሞላው ወይም አስቀድሞ ከቤተሰቡ ጋር ያለው ትስስር የጠነከረ መሆኑ ሲታመን የክትትል ሥራው ይቋረጣል፡፡

33. <u>ታዳጊዎችን ስለማቋቋም ወይም ከማህበረሰብ ጋር የማዋሀድ ሥርዓት</u>

1. ታዳጊዎችን ለማቋቋም መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፡-
   ሀ) ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆናቸው ታዳጊዎች፤
   ለ) ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ሆኗቸው የከፍተኛ ትምህርታቸውን ወይም የኮሌጅ ትምህርታቸውን ወይም የሙያ ሥልጠና ያጠናቀቁ፤
   ሐ) ዕድሜያቸው ከ15-18 ዓመት ሆኗቸው ቤተሰቦቻቸውን ወይም የቅርብ ዘመዶቻቸውን በማፈላለግ ሊገኙላቸው ያልተቻለ ተቋቁመው ለመውጣት ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑ ታዳጊዎች፤
   መ) በተቋም ውስጥ እየኖሩ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ትምህርታቸውን መቀጠል ያልቻሉ ወይምወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መግቢያ ውጤት ማምጣት ያልቻሉና የሙያ ሥልጠና ወስደው ያጠናቀቁ ታዳጊዎች፤
   ሠ) ከተቋሙ ተቋቁመው በመውጣት ወደ ማኅበረሰብ ተዋሕደው የራሳቸውን ሕይወት ለመምራት ዝግጁ የሆኑ ታዳጊዎች፡፡
2. ስለቅድመ-ማቋቋም ወይም ወደ ማኅበረሰቡ መዋሐድ
   ሀ) የማሳደጊያ ተቋሙ በበጀት ዓመቱ ተቋቁመው መውጣት የሚገባቸውን ታዳጊዎች ይለያል፤

ለ) የተቋሙ የማኅበራዊና ሥነ-ልቦና ቡድን የተለዩ ታዳጊዎችን የሥልጠና ፍላጎታቸውን ይለያል፣ መረጃቸውን ያደራጃል፣ እንዲሁም ወደ ሥልጠና ለመግባት ዝግጁ እንዲሆኑ ማመቻቸት ይኖርበታል፤

ሐ) በበጀት ዓመቱ የሚቋቋም ታዳጊ የራሱን የግል ዕቅድ በጽሑፍ አዘጋጅቶ በተቋሙ የማኅበራዊ ባለሙያ አማካኝነት ተገምግሞ ለተቋሙ ሲቀርብ በተቋሙ ማረጋገጫ ለቢሮው ሪፖርት ይደረጋል፤

መ) ቢሮውና ተቋሙ በጋራ በመሆን ታዳጊዎች እንደየፍላጎታቸው እና እንደየትምህርት ዝግጅታቸው በመረጡት ወይም በሚጋብዛቸው የሙያ ዘርፍ በቂ ሥልጠና እንዲወስዱ እና ለስልጠናው አስፈላጊውን ወጪ በመሸፈን ሥልጠናውን እስኪጨርሱ ድረስ በቂ የክትትልና የድጋፍ ሥራ ይሠራል፤

ሠ) የሙያ ሥልጠናውን በበቂ ሁኔታ ተከታትለው ሲያጠናቅቁ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ተቋሙና ቢሮው ክትትልና ድጋፍ ያደረጋል፤

ረ) ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች ቢሮው የሚያዘጋጃቸውን የተለያዩ የሥነ-ልቦና እና የማነቃቂያ ሥልጠናዎችን በበቂ ሁኔታ ተከታትለው በቢሮው የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

4. የስራ ዕድል ስለማመቻቸት

ሀ) ታዳጊዎች ከሚኖሩበት ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲያገኙ ቢሮውና የተቋሙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤

ለ) ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች የከተማው የወጣቶች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢሮው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሐ) ቢሮው ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች እንደየፍላጎታቸው ተደራጅተው እንዲሠሩ ያመቻቻል፣ የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

5. ወደ ማኅበረሰብ ማዋሐድ ሥርዓት

ሀ) በጀት ዓመቱ ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች ወደ ማኅበረሰቡ በሚዋሐዱበት ጊዜ በሚደረግላቸው ድጋፍ ላይ በተቋሙና በታዳጊዎች መካከል የስምምነት ፊርማ ይደረጋል፤

ለ) ተቋሙን የሚለቁ ወይም ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች የመቋቋሚያ ገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን ከመጠየቃቸው አስቀድሞ የሙያ ስልጠና ምስክር ወረቀት መያዝ ይጠበቅባቸዋል፤

ሐ) ተቋሙን የሚለቁ ወይም ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች በተቋሙ ውስጥ ምንም ዓይነት ዕዳ እንደሌለባቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

34. <u>የቁሳቁስ እና የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ</u>

1. ማንኛውም ከተቋሙ ተቋቁሞ የሚወጣ ታዳጊ የዩኒቨርሲቲ ወይም የኮሌጅ ትምህርት አጠናቀው ሥራ ሲይዙ ወይም ተቋም ውስጥ እየኖሩ በተለያዩ አጋጠሚዎች ሥራ ሲኖራቸው ፡-

   ሀ) የመኝታ ቁሳቁስ እንደ አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ ትራስ፣ ቁምሳጥን መግዣ የሚሆን የጥሬ ገንዘብ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፤

   ለ) የማዕድ ቤት ቁሳቁስ የማብሰያ፣ የመመገቢያ፣ የንፅሕና ቁሳቁስ መግዣ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ብር 8,000.00 /ስምንት ሺህ ብር/ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ ይሆናል፤

   ሐ) ታዳጊ ተቋቁሞ ከተቋሙ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ለቤት ኪራይ መደጎሚያ የሚሆን ጥሬ ገንዘብ ለ6 (ስድስት) ተከታታይ ወራት የሚሰጥ ይሆናል፤ በመጀመሪያው ሦስት ወራት በየወሩ ብር 4,000.00 /አራት ሺህ ብር/ የሚሰጥ ሲሆን ለቀጣዮቹ ሦስት ወራት ደግሞ በየወሩ ሃምሳ በመቶ (50%) ተቀናሽ ተደርጎ ማለትም ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) የሚሰጥ ይሆናል፤ በአጠቃላይ ለስድስት ወራት ለቤት ኪራይ መደጎሚያ የሚሰጠው ገንዘብ መጠን ብር 18,000.00 (አስራ ስምንት ሺህ ብር) ሆኖ ገንዘቡ በታዳጊው የግል የባንክ አካውንት ውስጥ በየወሩ ተሰልቶ ገቢ ይደረጋል፤

   መ) ተቋቁመው ሲወጡ ሥራ ላልነበራቸው ታዳጊዎች ለሥራ ማፈላለጊያ የሚሆን ብር 6,000.00 /ስድስት ሺህ ብር/ በጥሬ ገንዘብ ድጎማ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፤ታዳጊው በሚከፍተው የባንክ አካውንት በኩል ገቢ ይደረጋል፤

ሠ) ታዳጊዎች ተቋቁመው በሚወጡበት ጊዜ በከተማ መስተዳደሩ በሚደረግ የመኖሪያ ቤት ዕድል ተጠቃሚ ከሆኑ ለቤት ኪራይ መደጎሚያ ገንዘብ ብር 18,000.00 /አሥራ ስምንት ሺህ ብር/ ተጠቃሚ በድጎማ መልክ በጥሬ ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ይህ ክፍያ ተቋቁመው የወጡ ታዳጊዎችን አይመለከትም፤

ረ) የአካል ጉዳት ያለባቸው ታዳጊዎች ለሌሎች የተፈቀደውን ለመኝታ ቁሳቁስ እና ለማዕድ ቤት ዕቃ መግዣነት የሚውል የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን ለቤት ኪራይ መደጎሚያነት በተፈቀደው ገንዘብ ላይ የ20% ጭማሪ ተደርጎ ተቋቁመው ከወጡበት ቀን /ወር/ ጀምሮ ለ6 ተከታታይ ወራት በባንክ አካውንት ገቢ የሚደረግ ይሆናል፤

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተራ ፊደል (ረ) የተጠቀሰው የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታን በተመለከተ እንደአስፈላጊነቱ ስለአካል ጉዳተኝነቱ ከመንግስት የጤና ተቋም የሕክምና ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፤

ሸ) ተቋቁመው የሚወጡ ታዳጊዎች ግቢውን ለቀው በሚወጡበት ወቅት ቀድሞ ሲጠቀሙበት የነበረውን የራሳቸውን የመኝታ ልብስና ፍራሽ እንደ አስፈላጊነቱ ይዘው ሊወጡ ይችላሉ፤

ቀ) ተቋቁሞ የሚወጣ ታዳጊ ከተቋሙ በሚወጣበት ጊዜ የቤት ኪራይ ወጪ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ቤት መከራቱን በኮሚቴ በኩል ማረጋገጫ ይቀርባል፡፡

2. ስለ ድጎረ ማቋቋም ወይም ማዋሐድ

ሀ) አግባባዊ የሆነ የመቋቋም ሂደትን ተከትሎ ተቋቁሞ አንድ ጊዜ ከተቋሙ የወጣ ታዳጊ በምንም ዓይነት ሁኔታ ዳግመኛ ወደ ተቋም ተመልሶ እንዲኖር አይፈቀድም፤

ለ) ተቋሙ የታዳጊዎችን የመኖሪያ አድራሻ፣ የሚሠሩትን ሥራ፣ ለማቋቋሚያ ያገኙትን ድጋፎች የመሳሰሉ መረጃዎችን በማደራጀት በቀጣይ ለሚደረገው ክትትል ዝግጁ አድርጎ መያዝ ይኖርበታል፤

ሐ) ተቋቁመው ከግቢ የወጡ ታዳጊዎችን ተቋሙ በ6 ወር አንድ ጊዜ ክትትል በማድረግ ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ በመገንዘብ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደረጋል፤

መ) በበጀት ዓመቱ ተቋቁመው የወጡ ታዳጊዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉበትን ሁኔታ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ተቋሙ ክትትል አድርጎ በ6 ወር አንድ ጊዜ ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 35. የልደት ሠርተፊኬት

ቢሮው በሚያስተዳድራቸው ተቋማት ውስጥ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለሆኑ ሕፃናት ከወረዳው ወይም ክፍለ ከተማው ሴቶች፣ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ጋር በመሆን ለሚወጣላቸው የልደት ሠርተፊኬት አግባብ መሠረት ሕጋዊ ደረሰኝ ሲቀርብ አስፈላጊውን ወጪ ቢሮው ይሸፍናል፡፡

## 36. ስለ ጋብቻ

ቢሮው በሚያስተዳድራቸው ተቋማት ውስጥ ለሚኖሩ ታዳጊዎች ትዳር ለመመሥረት ዝግጁ መሆናቸውን በሚያሳውቁበት ጊዜ፡-

1. በሀገሪቱ ህግ መሰረት ዕድሜያቸው ለጋብቻ የደረሰ መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. ታዳጊዋ ተጠልፋ፣ በግዴታ ወይም ከፍላጎት ውጪ መሆን አለመሆኑን ያጣራል፣ ያረጋግጣል፤
3. በጋብቻ ለመተሳሰር ያለውን ሥነልቦናዊ፣ ሥነ ማኅበራዊ እና አካላዊ ዝግጁነትበተቋሙ የሥነ ልቦና እና ማኅበራዊ ሠራተኞች አማካኝነት ይጣራል፣ እገዛ ይደረጋል፤ቢሮው የታዳጊው የጋብቻ ሁኔታ ህጋዊ መሆኑን ሲያረጋግጥ እንደ ቤተሰብ ለጋብቻ ጠያቂ ሽማግሌዎችን ይቀበላል ይሸኛል፤
4. ለጋብቻ በተቆረጠው ቀን መሠረት ለድግስ የሚሆን ዝክረ-ተግባር ይዘጋጃል፤
5. ለቀለበት ሥነ-ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚሆን ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) ወጪ በማድረግ ለዕለት የቀለበት ሥነ-ስርዓት ዓላማ እንዲውል ይደረጋል፤
6. የቀለበት ሥነ-ሥርዓቱ ቢሮው በሚያዘጋጀው ዝክረ ተግባር መሠረት የሚከናወን ይሆናል፤
7. ከጋብቻ በኋላ ስለሚኖሩ ሥነ ልቦናዊ፣ ሥነ ማኅበራዊ እና አካላዊ ለውጦችና ዝግጅቶች በተቋሙ የሥነ ልቦና እና ማኅበራዊ ሠራተኞች የምክክር ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡

## 37. ሞት

ቢሮው በሚያስተዳድራቸው ተቋማት ውስጥ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሕፃናት ወይም ታዳጊዎች ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ እንደ ሃይማኖታቸው ሁኔታ:-

1. ሙሉ የቀብር ሥነሥርዓት ማስፈጸሚያ እና የዕለት ማስተዛዘኛ ወጪን በተቋሙ ተጠይቆ በቢሮው እውቅና ሰጥቶበት የሚፈጸም ይሆናል፤

2. ወጪው በወቅቱ የገበያ ሁኔታ መሠረት የሚቀርብ ሲሆን ለቀብር ሥነ ሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች /ሳጥን፣ ሰሌን፣ ለጉድጓድ ማስቆፈሪያ፣ ጥጥ፣ አቡጀዲ፣ ባዴጅ፣ ግላቭ፣ አልኮል፣ ለቀብር ማስፈጸሚያ መኪና፣ ለእምነት የቀብር ክፍያ፣ የድንኳን፣ ወንበር፣ የሰሀንና ኩባያ ኪራይ፣ የአስከሬን ሽቶ እና የመስተንግዶ ውኃ፣ እንጀራ፣ የንፍሮ እህል፣ ቡና፣ ሻይ፣ ስኳር፣ ቆሎ/ እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ቁሳቁሶች ሊጨመሩ የሚችል ሲሆን የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) የሚደጎም ይሆናል፤

3. የተቋሙ ታዳጊ የነበረ ነገር ግን ተቋቁሞ የወጣ ታዳጊ ከሆነና ወጪ መሸፈኑ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በቢሮው የበላይ ሀላፊዎች ታይቶ የሚወሰን ሆኖ ወጪው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ለ) በተደነገገው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት - ስለ ቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ አገልግሎት

38. ለነፍሰ-ጡር ሴቶች፣ አጥቢ እናቶች እና እድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሚደርሱ ሕፃናት ስለሚደረግ የቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ አገልግሎት

1. የተጠቃሚዎች መመልመያ መስፈርቶች የምከተሉት ናቸው፡-

   ሀ) በገቢ መጠናቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ አጥቢ እናቶች፤

   ለ) በገቢ መጠናቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ነብሰ ጡሮች እናቶች፤

   ሐ) በገቢ መጠናቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ እደሜቸው ከ0-3 ዓመት የሚሆኑ ሕፃናት ናቸው፡፡

2. የድጋፍ አሰጣጥ የአሰራር ሂደት

   ሀ) ተጠቃሚዎች መለየትና ማጽደቅ፤

   ለ) የመለያ መታወቂያ ማዘጋጀት፤

   ሐ) የጊዜ ሰሌዳን ታሳቢ ያደረገ ኮፖን ማዘጋጀት፤

   መ) ወረዳ በተሰራው ድልድል የደረሰውን ቁጥር ተጠቃሚዎች በመስፈርት መሰረት በመመልመል ለክፍለ ከተማ መላክ፤

   ሠ) ክፍለ ከተማ በወረዳ ተመልምለው የተላኩ ተጠቃሚዎችን መረጃ በማረጋገጥ ለማዕከል መላክ፤

   ረ) ከክፍለ ከተሞች ተረጋገጦ የመጣው የተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃው በማዕከል ተደራጅቶ ከፀደቀ በኋላ ለክፍለ ከተማ ኅብረት ስራ ሸማቾች እና ለሚመለከረታቸው አካላት የሚላክ ይሆናል፤

   ሰ) አገልግሎቱን እንዲሰጡ የተመረጡ በየክፍለ ከተሞች የሚገኙ ሸማች ማህበራት ለተጠቃሚዎች የአልሚ ምግቦችን በአይነቶች፣ በመጠን፣ በጥራት እና በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በየወሩ ሳይቆራረጥ እየተሰጠ መሆኑን በወረዳ ድረጃ ክትትል እየተደረገ ለክ/ከተማና ለማአከል ሪፖርት በማድረግ ማረጋገጥ፤

   ሸ) የተጠቃሚነት ሂደቱ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወቅታዊ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፡፡

39. <u>የባለ ድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት</u>

1. የቢሮው ሚና

   ሀ) ከቀዳማይ ልጅነት ፕሮጀክት አንፃር የአልሚ ምግብ ተጠቃሚዎች መስፈርትን ማዘጋጀት፤

ለ) በስራው ቀጥታ ተሳትፎ ያላቸውን ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤

ሐ) የአፈፃፀም መመሪያ የሚያስፈልጋቸው አሰራሮች መለየትና የአተገባበር መመሪያ ማዘጋጀት፤

መ) የአሰራር ስርዓቱን አፈፃፀም መከታተል፤ መገምገም እና ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤

ሠ) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ድጋፍን ማጠናከር፤

ረ) የድጋፍ ጊዜያቸው ያበቃ ተጠቃሚዎች በሂደቱ መሰረት ማሰናበት እና አዳዲስ ተጠቃሚዎችም እንዲለዩ በማድረግ መተካት፤

ሰ) አጠቃላይ የፕሮግራሙን አፈፃፀም በተመለከተ መረጃዎችን ማደራጀትና መያዝ፤

ሸ) ፕሮግራሙ በየደረጃው ያመጣውን ለውጥ መገምገም፤ ተሞክሮዎችን መቀመር እና ማስፋት፤

ቀ) ለነብሰ ጡር፣ ለሚያጠቡ እናቶችና ተንከበካቢዎች የሚቀርቡ አልሚ ምግቦችን ዝርዝር በተመለከተ የውስጥ አሰራር ማንዋል ያዘጋጃል፡፡

2. የክፍለ ከተማ የሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ሚና፡-

ሀ) በወረዳ ደረጃ የተመለመሉና የጸደቁ የአልሚ ምግብ ተጠቃሚዎችን መረጃ በማደራጀት ለማእከል መላክ፤

ለ) በወረዳ ደረጃ የሚከናወነውን የመለየትና የመፅደቅ ሂደት መከታተል፤

ሐ) አገልግሎቱ በሚጀምርበት ጊዜ ከወረዳ ጋር በመቀናጀት ክትትል ማድረግ እና ትክክለኛ አገልገሎት እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥና ለቢሮ ሪፖርት ማድረግ፤

መ) በየጊዜው አገልግሎቱ ያለበትን ደረጃ ለቢሮ ሪፖረት በማድረግ ማሳወቅ፡፡

3. የወረዳ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ሚና፡-

ሀ) ለአልሚ ምግብ ተጠቃሚ የሚሆኑ ነብሰጡር፣ አጥቢ እና ሕፃናትን በመስፈርቱ መሰረት ባሉት አደረጃቶችን በመጠቀም መለየት እና ማፅደቅ፤

ለ) የተለዩ እና የፀደቁ ተጠቃሚዎችን ሙሉ መረጃ መስብሰብና ማደራጀት፤

ሐ) መረጃዎችን ለክፍለ ከተማ መላክ፤

መ) በከተማ ደረጃ የሚዘጋጀውን የተጠቃሚዎች መለያ ወይም መታወቂያ፣ ኩፖን እና ሌሎች መረጃዎችን ለተጠቀሚዎች ማድረስ፤

ሠ) በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር አማካኝነት ለተጠቃሚዎች የሚደረገውን አገልግሎት መከታተል በግዜ፣ በአይነት፣ በጥራት ሳይቆራረጥ እየተከከናወነ መሆኑን መከታተል ማረጋገጥ፡፡

4. የተጠቃሚዎች ሚና

ሀ) ተጠቃሚዎች የተዘጋጀላቸውን መለያ በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፤

ለ) በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የአልሚ ምግብ ድጋፉ በሚሰጥበት ቦታ መገኘትና መረከብ ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የማኅበራዊ ችግር ተጋላጮችና ተጎጂዎችን ማቋቋሚያና ድጋፍ ስለመስጠት

40. ሰዉ ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ስለማድረግ፡-

1. ድጋፉን ለማድረግ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ለ. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልፅ የቀበሌ መታወቂያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ የነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸው ከሆነ ነዋሪነታቸውን የሚኖሩበት አካባቢ የማኅበረሠብ አቀፍና እንክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ በኩል እና በወረዳው ሴቶች፣ህፃናትና ማኀበራዊ ጉዳይ ፅህፈት ቤት በኩል ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፤

ሐ. ከሚኖሩበት ክ/ከተማና ወረዳ ችግረኛ መሆናቸውን የሚገልጽ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

መ. የህክምና ማስረጃ ለሚያስፈልጋቸው ሰዉ ስራሽ አካልና የአካል ድጋፍ አይነቶች ህጋዊ የህክምና ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

2. የሚደረገው ድጋፍ

ሀ. የጠየቁት የሰዉ ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ በቢሮው የሚሰጥ ይሆናል፤

ለ. በቢሮው ከሌለ የሰዉ ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ የበጎ አድራጎት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲያገኝ በየደረጃዉ ባለዉ ጽህፈት ቤት በኩል የድጋፍ ደብዳቤ ይጻፍላቸዋል፤

ሐ. ሰዉ ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ካልተገኘ በቢሮው እስከ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ ብር) ድረስ ግዥ ተፈጽሞ ድጋፉ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

መ. የኦርቶፔዲክስና ፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ከመንግስት የህክምና ተቋም በሚቀርብ ማስረጃ መሰረት ወጭውን ቢሮው ይሸፍናል፡፡

ሠ. በአካል መጥቶ ድጋፉን መዉሰድ ለማይችል ተገልጋይ በሚኖርበት ወረዳ ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት በኩል መረጃዉ ተረጋግጦ ለቤተሰቡ በወረዳ ባለሙያ በኩል ድጋፉ እንዲያገኝ ያስፈልጋል፤

41. የማዕከል አገልግሎት ስለመስጠት

1. ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነት መታወቂያ ያለው፤ የነዋሪነት መታወቂያ የሌለው ከሆነ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ የሚመለከታቸው አካላት ሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ

ጉዳይ እና የአካባቢው የማኅበረሠብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

ለ. በሌላ አማራጭ ሊደገፉ የማይችሉ መሆኑን በወረዳ ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያ እና በአካባቢው የማኅበረሠብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ ተጠንቶ በሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ለክፍለ ከተማው ሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ፅ/ቤት በማቅረብ የጽህፈት ቤት ኃላፊ የቀረበውን ማስረጃ አረጋግጦ በደብዳቤ ለቢሮ ማቅረብ አለበት፤

ሐ. ከክፍለ ከተማ ጽ/ቤት ኃላፊው በቀረበው ማስረጃ መሠረት የቢሮ ኃላፊው ለማህበራዊ ዘርፍ በመምራት በዘርፉ ባለሙያዎች ተገቢነቱ እንዲረጋገጥ ካደረገ በኋላ በቅድሚያ ከቢሮው ጋር የሁለትዮሽ ወይም የሶስትዮሽ ስምምነት ካደረጉ ድርጅቶች ጋር አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ ካለ እንዲያመቻቹ ካልሆነ ግን በቢሮው ስር ባሉ ተቋማት እንደ ተጎጂዎቹ እድሜና የአካል ጉዳት አይነትና መጠን አገልግሎት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ የውሳኔ ሀሳብ በዘርፍ ኃላፊው በኩል እንዲቀርብ ይደረጋል፤

መ. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም በቢሮው ስር ባሉት ተቋማት ውስጥ ተገልጋዩን ማስተናገድ የሚችል ቦታ መኖሩ ሲረጋገጥ፤

ሠ. ወደ ተቋም ሲገቡ የተቋሙን ማንኛቸውንም ተጨማሪ ግዴታዎች ሊቀበሉ የሚችሉ፤

ረ. ጧሪና ደጋፊ እንዲሁም ተጨማሪ ሀብት ቢኖራቸውና ይህም በተጨባጭ ማስረጃ የሚረጋገጥ ከሆነ ቢሮው ተገቢ የሚለውን እርምጃ እንደሚወስድ የሚቀበሉ ከሆነ፤

ሰ. አካል ጉዳተኞች መሆናቸዉና የጉዳታቸዉ መጠን በህክምና ማረጋገጥ ሲችሉ፡፡

ሸ. በቢሮው ስር ባሉ ተቋማትም ይሁን ከቢሮው ጋር ስምምነት ለተፈራረሙ በጎ አድራጎት ማህበራት የሚላኩ ተገልጋዮች በቢሮው እውቅና ብቻ መሆን አለበት፤

ቀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ሀ) ላይ የተጠቀሠው በቢሮው የሚመለከተው የስራ ክፍል በኩል ተፈፃሚ ይሆናል፤

በ. በየደረጃው ባለው መዋቅር እየተረጋገጡ የመጡትን ሙሉ ማስረጃዎች ኮፒ በማያያዝ አገልግሎቱን በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ለሚሰጠው ተቋም እንዲቀበል የድጋፍ ደብዳቤ በቢሮው በኩል ብቻ በመፃፍ እንዲገቡ ይደረጋል፤

ተ. ከቢሮ የተፃፈውን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ተገልጋዩን ወደ ተቋሙ የሚያስገባው ለተቋሙ ጥያቄዉን ያቀረበዉ ተቋም ነዉ፡፡ ለ.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ሀ) ላይ የተጠቀሠው በቢሮው የሚመለከተው የስራ ክፍል በኩል ተፈፃሚ ይሆናል፤

2. የሚደረገው የድጋፍ አይነት

ሀ. ተገልጋዩ ወደ ተቋሙ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በተቋሙ የሚሠጡ አገልግሎቶችን በስታንዳርዱ መሠረት እንዲያገኝ ይደረጋል፤

ለ. በጊዜያዊነት የተቋም አገልግሎት አግኝተው ላገገሙ ተገልጋዮች በተዘጋጀው ኖርም መሰረት የመቋቋሚያ፣ የስልጠናና የስራ መረጃና የግብአት ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ይደረጋል፡፡

42. ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የመብት ማህበራት ድጋፍ ስለመስጠት

1. ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. ማህበራቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የተመሰረቱ ከሚመለከተው የመንግስት አካላት የምዝገባ ፍቃድ ሰርተፍኬት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ. ከሚመለከተው የመንግስት አካላት ወቅቱን የጠበቀ የምዝገባ ሰርተፍኬቱ እድሳት የተደረገለት መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ. የአካል ጉዳተኛ ማህበሩ የተለያየ የአካል ጉዳት ዓይነት ያለባቸውን አባላትን ያካተተ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ. የሚሰጠውን የድጋፍ አይነት ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆነ፤

ሠ. የሚፈልጉትን የድጋፍ አይነት በማህበሩ በኩል በፊርማ ተረጋግጦ ጥያቄ ሲቀርብ፡፡

2. የሚደረገው የድጋፍ አይነት

ሀ. የመብት ማህበራት (የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን ማህበር) አመታዊ ጉባኤ ሲያካሂዱ ለእያንዳንዳቸው ማህበር የተሳታፊዎችን ወጪ ቢሮው በዓመት አንድ ጊዜ እስከ ብር 200,000 (ሁለትመቶ ሺህ ብር) ይሸፍናል፤

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ሀ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለከተማው የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን የመብት ማሕበራት በየዓመቱ ለእያንዳንዳቸው ብር 100, 000(መቶ ሺ) በጥሬ ገንዘብ በማህበራቱ የባንክ የሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚደረግ ይሆናል፤

43. አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ስለማበረታታት

1. አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ለማበረታታት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. በትምህርት ሚኒስቴር የነጥብ ደረጃ መሰረት በበጀት አመቱ ወደ ዩንቨርሲቲ መግቢያ የመቁረጫ ነጥብ ያመጡ መሆናቸው ሲረጋገጥ፤

ለ. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልፅ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የሚማሩበት ትምህርት ቤት መታወቂያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ የነዋሪነት መታወቂያ የሌላቸው ከሆነ ነዋሪነታቸውን ከሚኖሩበት አካባቢ የማኅበረሠብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ በኩል እና በወረዳው ሴቶች፣ህፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ፅህፈት ቤት በኩል ማረጋጫ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ፤

ሐ. ቢሮው የሚሰጠውን ድጋፍ ለማግኘት በውክልና ለሚጠይቁ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ውክልናውን የሚያስረዳ ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

መ. የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በበጀት አመቱወደ ዩንቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ያመጡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መረጃ ለሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ መላኩ ሲረጋገጥ፤

ሠ. ቢሮው የሚሰጠውን ድጋፍ ለመውሰድ ፍቃደኛ የሆኑ፡፡

2. የሚደረገው የድጋፍ አይነትና መጠን

ሀ. አልባሳት ድጋፍ ለአንድ ጊዜ ብቻ (ብርድ ልብስ፣አንሶላና ትራስ ጨርቅ፣ቱታ፣የሌሊት ልብሶች፣ፎጣ፣የንፅህና መጠበቂያ እና ቦርሳ) ድጋፍ ይደረጋል፤

ለ. የገንዘብ ማበረታቻ ለአንድ ጊዜ ብቻ ለአንድ ሰው ብር 20,000 (ሀያ ሺህ ብር) ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

44. የማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ስለማቋቋም

1. ሊያሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ መሆኑን የሚገልፅ የነዋሪነት መታወቂያ ያለዉ ወይም የነዋሪነት መታወቂያ የሌለው ከሆነ ከወረዳ የሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ እና የአካባቢው የማኅበረሠብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

ለ. በከተማ አስተዳደሩ ዉስጥ የሚገኙ መንግስታዊ መዋቅር የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ የማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች በሚከናወነዉ የልየታ ስራ ያለፈ

ምንም አይነት የገቢ ምንጭ የሌላቸው፣ በእድሜ መግፋት፣በአካል ጉዳት ፣በጤና መታወክ፣ ምንም ረዳት፣ ተንከባካቢና ደጋፊ እንደሌላቸው ከሚኖሩበት ወረዳ ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት እና የአካባቢው የማኅበረሠብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ኮሚቴ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ማረጋገጥ ሲቻል፤

ሐ. የሚሰጠውን የተሃድሶ ሙያ ስልጠናና የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ለመግባት ፈቃደኛ የሆኑና የማዕከሉን መተዳደሪያ ደንብ የሚያከብሩ፤

መ. የሚሠጠውን የክህሎት ስልጠና አጠናቆ ብቁ የሆነ፤

ሠ. በሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ በግል ወይም በማህበር ተደራጅቶ ወደ ስራ ለመሰማራት ፍላጎቱ ያለው፤

ረ. መንግስታዊ ተቋም እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የድጋፍ ተጠቃሚ ያልሆኑ፤

2. የሚደረገው የድጋፍ አይነትና መጠን

ሀ. ወደ ክህሎት ስልጠና ከመግባቱ በፊት በቋሚ መድረክ የምክር፣ መረጃና ግንዛቤ ማሻሻያ ድጋፍ በማህበራዊ ዘርፍ ባለሙያዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በጋራ በመተባበር የሚሰጡ አገልግሎቶች የስነ-ልቦና፣ የህይወት ክህሎት ስልጠና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ. በመረጠው የስራ መስክ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ሐ. የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በየቀኑ የትራንስፖርት ክፍያ በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ አሰራር ስርአት መሠረት እንዲከፈል ይደረጋል ወይም በጋራ ለማጓጓዝ የከተማ አውቶቡስ ቢሮው ይመቻቻል፤

መ. ስልጠናውን በአግባቡ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ በከተማው አስተዳደር የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ በኩል የስራ ዕድል እንዲያገኝ ዝርዝር መረጃው ይላካል፣ ተጠቃሚ እንዲሆኑም አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤

ሠ. የሙያ ብቃት ምዘና ወስደው በማህበር እንዲደራጁ ድጋፍ ይደረጋል፣

ረ. ለሙያ ብቃት ምዘና የአገልግሎት ክፍያ ከተቋሙ በሚቀርበው ጥያቄ ተያይዞ በሚቀርበው የሠልጣኝ ዝርዝር መሠረት በቢሮው በኩል ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፤

ሰ. የብቃት ማረጋገጫውን ወስደው ላላለፉ ተፈታኞች ተጨማሪ አንድ እድል ተሰጥቷቸው እንዲፈተኑ ይደረጋል፤

ሸ. በመረጡት የሥራ ዘርፍ መሰረት መሰማራት ለሚፈልጉ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ለከፋ የምግብ ችግር የተጋለጡ ነዋሪዎች፣ለምኖ አዳሪዎች፣ በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩና አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚዎች ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸዉ በሚያቀርቡት የስራ እቅድ መሰረትበግል 40,000.00 (አርባሺህ ብር) የአይነት ድጋፍ ይደረጋል፤

ቀ. በማህበር ተደራጅቶ የማቋቋሚያ ድጋፍ ለሚጠይቅ ማህበር ለአንድ ሰው የሚደረገው የብር መጠን ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) ሲሆን ይህም በአባላት ቁጥር ተሰልቶ በሚመጣው የገንዘብ መጠን የአይነት ድጋፍ ይደረጋል፤

በ. ቀጣይነት ባለው መልኩ ድጋፍና ክትትል እንዲያገኙ በማድረግና መረጃዎችን በማዘመን በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡

45. **የባይተዋር ቀብር አገልግሎት**

1) ሊሚሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. የባያተዋር ቀብር ተጠቃሚዊች መሆናችው በሆስፒታሎች መረጋገጥ ሲቻል፤

ለ. ምንም አይነት ቀባሪ የሌላችውና አድራሻቸው የማይታውቅ መሆኑ ማረጋገጥ፣

2) የሚደረገላቸው የድጋፍ አይነት

ሀ. የባይተዋር ቀብር ተጠቃሚዎች መሆናችው በሆስፒታሎች ሲረጋገጥ የማቹን አስክሬን የሚየሽፍን የከፈን አቅርቦት ማድረግ፤

ለ. የሟቹን ማንነት የሚገልፅ ሙሉ ስም፤ የሞተበትን ቀንና አመት የሚገልጽ ታፔላ አቅርቦት ድጋፍ ማድረግ፡፡

46. ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች ማቋቋምና ድጋፍ አሰጣጥ

1) የማቋቋሚያ ድጋፉን ለማግኘት ሊያሚሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ. በማቋቋም ፕሮግራም ምዝገባና ልየታ ሂደት ውስጥ አልፈው የስነ-ልቦናና የሕይወት ክህሎት ስልጠና የወሰዱ፤

ለ. የሚሰጠውን የተሃድሶ (የስነ-ልቦና፣ የሕይወትናየሙያ ክህሎት) ስልጠና ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆነ፤

ሐ. ከተማ አስተዳደሩ በሚያመቻቸው ማንኛውም ድጋፍ ተጠቅሞ ራሱን ለመለወጥ ዝግጁ የሆነ፤

መ. ወደመጡበት ክልል/አካባቢ/ ቤተሰብ ተመልሰዉ በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑ፤

ሠ. የመጡበትን አካባቢ ሙሉ መረጃ አድራሻ (ዞን ፣ ወረዳ ፣ ቀበሌና) ማሳወቅ የሚችሉ፤

ረ. የሚገባባትን ማገገሚያ ማዕከል የውስጥ ዲሲፕሊን ለማክበርና ከሌሎች ጋር ተባብሮና ተከባብሮ ለመለወጥ ፈቃደኛ የሆነ፤

ሰ. ዜጎችን የመመለሱ ሂደት የሚተገበረው ከመጡበት ክልል ጋር መግባባት ላይ ሲደረስ ብቻ ይሆናል፤

ሸ. ከዚህ በፊት በተመሳሳይ መልኩ ድጋፍ ያላገኙ መሆኑ ሲረጋገጥ፡፡

2. የሚደረገው የድጋፍ አይነትና የገንዘብ መጠን

ሀ. በጊዚያዊ ማገገሚያ ማዕከል በሚቆዩበት ወቅት የሚያስፈልግ የምግብ፣ የጤና አጠባበቅ የአልባሳትና ተያያዥ ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች እስኪሸኙ ድረስ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ. የድጋፍ ዓይነት ከትራንስፖርት ጋር የተያያዘ ከሆነ የሚመለሱበትን ቦታ መሰረት አድርጎ በሚቀርበው መረጃመሰረት በወቅቱ የትራንስፖርት ዋጋ እና የቦታውን እርቀት ግምት ውስጥ በማስገባት የመኪና መጓጓዣ ወጪ ትኬት ተገዝቶ እንዲሰጥ ይደረጋል ወይም ብዛት ያላቸው ከሆነ ቢሮው የትራንሰፖርት ማጓጓዣ በመከራየት አገልግሎት ይሰጣል፤

ሐ. አስፈላጊውን የተሃድሶ ስልጠና ወስደው በፍላጎታቸው መሰረት ወደ መጡበት አካባቢ መቀላቀልና ቤተሰብ መመለስ ወይም ሰልጥነው በተለያዩ የስራ ዕድል አማራጮች ተሰማርተው ገቢ ማግኘት እስኪችሉ ድረስ በማገገሚያ ተቋሙ ውስጥ የመጠለያ፣ የምግብ፣ የአልባሳት፣ የህክምናና የተለያዩ የስነ-ልቦና ድጋፎችን እስከ ስድስት (6) ወራት እንዲያገኙ ይደረጋል፤

መ. ወደ ቀያቸው እስኪደርሱ ድረስ የሚያስፈልግ የምግብ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ለአንድ ሰው ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይደረጋል፤በተጨማሪ ተቋቋሚው ወደ ስራ እንዲሰማራ የባንክ አካውንት

ተከፍቶ በነፍስ ወከፍ ለአንድ ጊዜ ብቻ ብር 4,000 (አራት ሺ ብር) ቢሮው ድጋፍ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

3. ተቋቋሚው የአዲስ አበባ ነዋሪ ከሆነ፡-

ሀ. የተቋቋሚውን አድራሻ በመለየት ቤተሰቡ/አካባቢው ላይ ገፊና አጋላጭ የሆኑ ምክንያቶች ላይ በመስራት በዚህ መመሪያ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 2 ከተራ ፊደል ሀ - ሐ የተቀመጠውን ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ. የሙያ ክህሎት ስልጠና ለሚወስዱ የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ አስፈላጊው ግብዓት በሟሟላት ብቁ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

ሐ. በከተማ አስተዳደሩ መንግስትና በግል ድርጅቶች ተፈላጊውን መስፈርት ላሟሉ የቅጥር ስራ ዕድል እንዲመቻች ፍራሽ፣ አንሶላና ብርድ ልብስ በዓይነት ድጋፍ በማድረግ ከማገገሚያ ማዕከላት እንዲለቁ ይደረጋል፣ ከተቀጠሩበት ተቋማት ጋር መረጃ በመለዋወጥ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤

መ. በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ወስደው ብቁ የሆኑትን በግል (በቅጥር) ወይም በማህበር ተደራጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ሲደረግ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 3 ተራ ፊደል ሀ ላይ የተቀመጠው ድጋፍ በነፍስ ወከፍ የሚሰጥ ሆኖ በተጨማሪ በማህበር ለተደራጁት እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ድጋፎችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 47. ድጋፍ ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

1) ሕፃኑ በሌሎች የክብካቤ አማራጭ አገልግሎቶች ተጠቃሚ የሚሆን ከሆነና ተጠቃሚነቱ ከተረጋገጠ፤
2) ተጠቃሚው ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ሲሆን እና ራሱን የሚችልበት ሁኔታ ሲመቻችለት፤
3) የተጠቃሚ ሕፃናቱ ወይም የወላጆቻቸው ወይም የአሳዳጊዎቻቸው ወይም የተንከባካቢዎቻቸው የገቢ መጠን ተሻሽሎ ሕፃናቱን ለማሳደግ በቂ ሆኖ ሲገኝ እና በገቢ ራሳቸውን መደገፍ ሲችሉ፤
4) ተጠቃሚው ሕፃን ተማሪ ከሆነ በሥነ-ምግባር ግድፈት ያለበትን የትምህርት ደረጃ በገዛ ፈቃዳቸው መማር ካቆሙና ለመማር ፈቃደኛ የማይሆኑ ሆኖ ሲገኝና በመረጃ ሲረጋገጥ፤
5) ተጠቃሚው በከባድ የስነ-ምግባር ግድፈት ማለትም አስገድዶ መድፈር፣ ወሲባዊ ጥቃት ማድረስ፣ ከባድ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ማጅራት መምታት፣ ከባድ አካላዊ ጥቃት ማድረስ፣ ድምፅ ያለው ወይም ድምፅ አልባ ጎጂ መሳሪያዎችን ይዞ መገኘት፣ የአደንዛዥ እፅ ሱሰኝነት፣ ድብደባና አምባጓሮ መፍጠር እና ሌሎች ተመሳሳይ ከባድ ጥፋቶች ሲፈፅም፤
6) ተጠቃሚ ሕፃናቱ በተለያዩ ምክንያቶች የመኖሪያ አድራሻ ከቀየሩና ለድጋፍና ክትትል አስቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ፤
7) ተጠቃሚ ሕፃኑ ከሀገር ከወጣ ወይም በሞት ከተለየ ድጋፉ ይቋረጣል፡፡

### 48. <u>የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት</u>

1. ድጋፍ የሚደረግላቸው ተጠቃሚዎች በአሰራር ሂደት ውስጥ ቅሬታ ሲኖራቸው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለወረዳ፣ ለክፍለ ከተማ እና ለቢሮ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፤
2. በወረዳም ሆነ በክፍለ ከተማ ደረጃ ለሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የቀረበው ቅሬታ በሶስት (3) ቀናት ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤

3. በክፍለ ከተማ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ለቅሬታቸው በሚሰጠው ምላሽ ያልረኩ አካላት አቤቱታቸውን ለቢሮ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ቢሮውም ለቀረበው ቅሬታ በአምስት(5) የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፣ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፤
4. የቀረበው ቅሬታ በቢሮ ደረጃ ብቻ የተፈጠረ ቅሬታ ከሆነ ቅሬታ አቅራቢዎች በቢሮው በተዘረጋው መደበኛ የቅሬታ አፈታት ስነ-ሥርዓት መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

49. **ኮሚቴ ስለማቋቋም**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹትን ተግባራት ተፈጻሚ ለማድረግ ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ ኮሚቴ ማዋቀር ወይም ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

50. **ስለ ክትትልና ድጋፍ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹትን ተግባራት ተፈጻሚ ለማድረግ ቢሮው ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

51. **የመተባበር ግዴታ**

የሚመለከተው አካል ሁሉ ይህን መመሪያ በማስፈፀም ረገድ ኃላፊነታቸዉን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፡፡

52. **ስለተጠያቂነት**

1. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው፣ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናል፤
2. ማንኛውም ሰው ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ውጭ የሰራ ወይም መመሪያው በአግባቡ እንዳይፈፀም ያሰናከለ ወይም ለተጠቃሚዎች የሚሰጠውን ሌሎች ድጋፎች ለግል ጥቅሙ ያዋለ አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

53. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ መመሪያዎች</u>

1. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ቢሮው ያወጣቸው መመሪያዎች እና አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡
2. ከዚህ በፊት በስራ ላይ የነበረው "ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ መመሪያ ቁጥር 133/2015" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

54. <u>መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን</u>

ቢሮው ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

55. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ ሚያዝያ 2018 ዓ.ም**

**ቆንጂት ደበላ ዋላ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ**